ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ
Wisdom at the Source of the Blue Nile

# ናይል
# THE NILE



ኢ-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

2ኛ ዓመት፣ ቁጥር 10፣ ሕዳር 2007

## የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በድምቀት ተከበረ

## ለጎ ሀይቅ - በአንድ ፊት፣ ሁለት መልክ

ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)

## እኔ እንዲህ እላለሁ!

አበባው ይርጋ (ዶ/ር)

## የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

ፈታሒ በቃሉ

## የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በራዕይ ጥበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)



US Embassy grants New Visa Class to BDU's Maritime cadets (from left to right - Jordon Buchler, General Manager of the Academy, Dr. Baylie Damtie, BDU's President, HE Patricia M. Haslach, U.S. Ambassador to Ethiopia and Mr. Dane Robbins, C1/D Visa Section Head)





የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደር ጉዳዮች ም/ፕሬዚደንት ዶ/ር እያዩ ሞላ የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዩኒቨርሲቲው ሲከበር ንግግር ሲያደርጉ

እውነትን መፈለግና ስሌሳው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

ናይል
THE NILE

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ

የአማካሪ ቦርድ አባላት
አቶ ሞገስ አብርሃ
ዶ/ር ጌታቸው ፍስሃ
ዶ/ር ጥጋብ በዜ
ዶ/ር እንየው ታደሰ
አቶ በላይነህ ወረቁ
ወ/ሪት እንዳስ ቃሶ
አቶ ፈታሒ በቃሉ
አቶ ብሩክ ከተማ
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

ዋና አዘጋጅ:-
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

ም/ዋና አዘጋጆች
ሀሰን ዑስማን
ሂሩት አድማሱ

አርታኢዎች
አብነት ሰለሞን
ነብዩ ንጉሴ

ዘጋቢዎች:-
አምሳሉ ጥላሁን
የማነ ገብሩ
ታድዬ አስማረ
ትግስት ዳዊት
አበባ ሐብቱ
ሙሉጎጃም አንዷለም

አምደኞች:-
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ፈታሒ በቃሉ
ሂሩት አድማሱ
ጀማል ሙሀመድ (ዶ/ር)
አበባው ይርጋ (ዶ/ር)
ተመስገን በየነ
አረጋዊ ሰለሞን

ግራፊክስና ሌይአውት:-
ፀጋነሽ ሙሉጌታ
ዘካርያስ ጋሹ

ፎቶ አንሺዎች:-
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

የኮምፒውተር ጽሁፍ:-
ፋንታነሽ ላቀው
ታሪክ ታደሰ
የሻለም መንግስቱ

ትራንስፖርት:-
ማናለ ኃይሌ
መልእክተኞች:-
ቃልኪዳን አወቀ
ንብረት ታፈረ

ስልክ:- +251 583206088

# አበይት ዜናዎች

## ዩኒቨርሲቲዎች ሙስናን የሚጸየፍ ትውልድ ከመቅረጽ አንጻር ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳላቸው ተጠቆመ

ትዕግስት ዳዊት

‹‹ለህዳሲያችን ስኬት በእውቀት፣ በክህሎትና በስነ-ምግባር የታነፀ ወጣት እናፈራለን›› በሚል መሪ ቃል የፌዴራል የስነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር አመታዊ ጉባኤውን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ አካሄደ፡፡ በጉባኤው ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ዩኒቨርሲቲዎች ሙስናን የሚፀየፍ ትውልድ የማፍራት አደራ እንዳለባቸውና የወደፊት አገር ተረካቢ የሆኑት ወጣቶችም ጥሩ አሻራ የሚያስቀምጡ ዜጎች እንዲሆኑ ለማድረግ መሥራት አለብን ብለዋል፡፡

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት አፈ ጉባኤ እና የክልሉ ፀረ-ሙስና ጥምረት ኃላፊ የተከበሩ አቶ ያለው አባተ በበኩላቸው ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል እና ለመዋጋት እንዲሁም ሙስናን የሚፀየፍ ህብረተሰብ ለመፍጠር በወጣቶች ዙሪያ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡ ከመማር ማስተማር ጎን ለጎን ከፍተኛ ትምህርት ተቋማትም ይህን ተግባራዊ ከማድረግ አንጻር ሀላፊነታቸውን መወጣት እንዳለባቸው ጠቁመዋል፡፡

በጉባኤው ላይ ከ32 ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ የፀረ-ሙስናና ሥነ-ምግባር ክበባት አመራሮች፣ የዩኒቨርሲቲዎቹ የስነምግባርና ፀረ-ሙስና ሃላፊዎች የተገኙ ሲሆን የስነ-ምግባርና ሙስና ጽንሰ ሃሳብ ከወጣቶች አንጻር፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ያሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች እንዲሁም መልካም አስተዳደር ከማስፈንና ሙስናን ከመዋጋት አንጻር የአመራሮች ሚና በሚሉ ርዕሶች ላይ ፅሑፎች የቀረቡ ሲሆን ከተሳታፊ ተማሪዎችም የተለያዩ ጥያቄዎች ተነስተው ውይይት ተካሂዷል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ የጉባኤው ተሳታፊዎች የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማሪታይም አካዳሚን የጎበኙ ሲሆን በአካዳሚው የሚሰለጥኑ ሰልጣኞች ለሙያቸው ያላቸውን ስርአትና የስነ ምግባር ተሞክሯቸውን በአካዳሚው መምህራን ገለጻ ተደርጎላቸዋል፡፡

## ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሕዝብን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል እያደረጉት ያሉት ተግባር ተደነቀ

አበባ ሐብቱ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ኢኮኖሚክስ ምርምር ተቋም በአማራ ክልል በሚገኙ ከተሞች ያለውን ዘርፈ ብዙ የድህነት ሁኔታ አስመልክቶ አውደ ጥናት አካሄደ፡፡
ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በየአካባቢያቸው የሚታዩ ችግሮችን በጥናት በመለየት የሚያከናውኑት ተግባር የሕዝብን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል የላቀ ጠቀሜታ እንዳለው የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳደር የተከበሩ አቶ ገዱ አንዳርጋቸው ተናግረዋል፡፡

ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየአከባቢያቸው የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት የጀመሩትን ተግባራት አጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚገባ በማሳሰብ በአውደ ጥናቱ ላይ የቀረበው ፅሁፍ ዩኒቨርሲቲው እያከናወነ ያለውን ተግባር ማሳያ ነው ያሉት ርዕሰ መስተደድሩ በአማራ ክልል በሚገኙት ከተሞች ያለውን ዘርፈ ብዙ የድህነት ሁኔታ አስመልክቶ የተካሄደው ጥናት አሁን በተጨባጭ የሚታዩትን ክፍተቶች የሚያሳይና በቀጣይ ምን መሰራት እንዳለበት የሚጠቁም መሆኑን ተናግረዋል፡፡
የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ኘሬዝዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው እንደተናገሩት ዩኒቨርሲቲው በምርምርና በጥናት ላይ የተመረኮዘ የፖሊሲ ጥናት ሐሳቦች በማመንጨት የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት እየሰራ እንደሚገኝ፣ በአሁኑ ወቅት የኢኮኖሚክስ የምርምር ተቋም በክልሉ ላይ ባሉ ችግሮች ላይ ምርምር እያካሄድ ችግሮችን ለመፍታት እየተንቀሳቀሰ እንደሆነና ችግሮቹን ለመቅረፍ ከሌሎቹ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋራ እንደሚሰራ ተናግረዋል፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ የኢኮኖሚክስ ምርምር ተቋም ተመራማሪ ዶ/ር ዳረጎት በሪሁን ጥናት በተደረገባቸው ከተሞች ላይ ያለው የድህነት ሁኔታ በተለያዩና አዲስ መለኪያዎች የሕብረተሰቡን የኑሮ ደረጃ የሚዳስስ ሲሆን በቀጣይ በጥናቱ የተገኘውን ሃሳብ መሠረት በማድረግ ለፖሊሲ ቀረፃና በእውቀት ላይ የተመሠረተ እቅድ ለማዘጋጀትና ለመስራት እንደሚረዳ ተናግረዋል፡፡ በአማራ ክልል ከተሞች በዋናነት የሕብረተሰብን የኑሮ ደረጃ ሁኔታ ለማወቅ የተጠናው ጥናት በአይነቱ የመጀመሪያ ሲሆን ጥናቱን ለማዳበር በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በተጠራው የአንድ ቀን አውደ ጥናት በክልሉና ከክልሉ ውጭ የሚገኙ የሚመለከታቸው ባለሙያዎችና የመንግስት ሃላፊዎች እንዲሁም የተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ምሁራን ተገኝተዋል፡፡

የኢኮኖሚክስ የምርምር ተቋም ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎት ላይ አትኩሮት በመስጠት እየሰራ እንደሚገኝ፤ በ2025 በአፍሪካ ውስጥ ካሉ የኢኮኖሚክስ የምርምር ተቋማት ውስጥ አንዱ ለመሆን ራዕይ ሰንቆ እየሰራ ያለና ቀጣይነት ያለው ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት በክልሉም ሆነ በሀገሪቱ ላይ እንዲኖር በሚደረገው ጥረት ላይ አስተዋጽኦ በመውሰድ እየሰራ ያለ ተቋም ነው፡፡

## የባሕል አውደ ጥናት ተካሄደ

ሙሉጎጃም አንዱዓለም

የባሕርዳር ዩኒቨርሲቲ ሂዩማኒቲስ ፋኩልቲ በኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል ባህላዊ ገፅታ ላይ የሚያተኩር ትምህረታዊ አውደ ጥናት አካሄደ፡፡ በአውደ ጥናቱ ላይ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ባህል የሚያሳይ የፎቶ ግራፍ አውደ ራዕይ ቀርቧል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ እንደተናገሩት ባህል የማህበረሰቡን ሃገር በቀል እውቀት እንዲሁም የእያንዳንዱ ሠው ማንነት መገለጫ በመሆኑ እንዲሁም የሚታዩና የማይታዩ መገለጫዎች ስላለው ጥናቶች የእያንዳንዱን ባህል ምንነት ላይ የሚያተኩሩ እና በግልጽ የሚያሳዩ መሆን አለባቸው፡፡ ዩኒቨርሲቲው የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመሆን የሠነቀውን ራዕይ እውን ለማድረግ አዲስ የስራ ባህል እንዴት መፍጠር እንደሚቻል እንዲሁም ዩኒቨርሲቲውን አጉልቶ የሚሳይ የባህል ጥናት በቀጣይነት እንዲቀርብ አሳስበዋል፡፡

በአውደጥናቱ ላይ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔርሰቦች እና ህዝቦች በዓል ላይ የተሳተፉት የተለያዩ ብሔሮች ቅኝት እና የስብጥር ፋይዳ፣ ጥበባትና ቁሳዊ ባህሎች፣ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል ስለስብጥረ-ባህል ያለውን ፋይዳ አስመልክቶ ፅሁፍ የቀረበ ሲሆን የቋንቋ፣ የልማድ፣ የሀይማኖት፣ ወዘተ... ትውውቅ እና ትስስር ለመፍጠር፣ ሀገራዊ ስሜትን እና ብሔራዊ መግባባትን ለማጠናከር፣ የሥራ ፈጠራን ለማበረታታትና ተወዳዳሪ ሆኖ በመገኘት የቱሪስት መስህብ ሀብቶችንና፣ ባህላዊ እሴቶችን ለማስተዋወቅ፣ ብሎም ታሪክን በማስተላለፍና ስነ-ልቦናዊ ደስታን ለማግኘት እንዲሁም ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ግንኙነትን ለማጠናከር ወሣኝ ሚና እንዳለው ተገልጿል፡፡

የፎክሎር (የባህል) ትምህርት ለዩኒቨርሲቲው ያለው ፋይዳ የላቀ እንሆነና ለወደፊት የሁሉንም ባህል በተናጠል ማየትና በተሻለ መልኩ መስራት እንደሚገባ የአውደ ጥናቱ ተሳታፊዎች ገልፀዋል፡፡ ባህል የማህበረሰቡን መንፈሳዊና ቁሳዊ ሃብቶች፣ ቋንቋ፣ ታሪክና ህልውና ወዘተ... የሚመራመሩበት፣ የሚሠነዱበት፣ የሚያድጉበትና ለልማት የሚውልበት ስልትና ባህላዊ እውቀት የሚጠናበት ሙያ መሆኑ ተገልጿል፡፡

To follow the latest news about BDU, check out our website:- **http://www.bdu.edu.et** or facebook address:- **www.facebook.com/bduethiopia**

# መልዕክቶችና አስተያየቶች

## ርዕሰ-አንቀጽ

### አገራዊ ለውጥ ለማምጣት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የድርሻቸውን እንዲወጡ እንደግፋለን!!!

ዘጠነኛው አገር አቀፍ የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ርዕሰ መዲና አሶሳ ህዳር 29 ቀን 2007 ዓ.ም በድምቀት ተከብሯል፡፡ ክብረ በዓሉ ‹‹በህገ መንግስታችን የደመቀ ኢትዮጵያዊነታችን ለህዳሴያችን›› በሚል መሪ ቃል በህዝቦች ሁለንተናዊ ዕድገትና የጋራ ተጠቃሚነት ዙሪያ ትኩረቱን አድርጎ ተከናውኗል፡፡

የህዝቦች የጋራ ቃልኪዳን የታደሰበት የዘንድሮው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ቀን በዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ አባላት ዘንድ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ተከናውኗል፡፡ ዕለቱ በዋናው ግቢ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በተለያዩ ክንውኖች ደምቆ ውሏል፡፡ የትውልድ ባለአደራ የሆነው ወጣቱ ክፍል የመጣበትን ማህበረሰብ በሚወክል አልባሳት ደምቆና በባህላዊ ጭፈራዎችና ውዝዋዜዎች አሸብርቆ የዕለቱን ፋይዳ ለማጉላት ጥሯል፡፡ ለህገራዊ አንድነቱ መጠናከር እና ለህዝቦች የጋራ ተጠቃሚነት መረጋገጥ የበኩሉን አስተዋጽኦ ለማበርከትም ቃልኪዳኑን አድሷል፡፡

‹‹ትልቅ ነበርን ትልቅ እንሆናለን›› በሚል መንፈስ የሀገራችንንና የህዝቦቿን ትንሳኤ ለማረጋገጥ የተጀመረው ውጥን መልካም አፈፃፀም ባሳየበት ማግስት የተከበረው የዘንድሮው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል ከሌሎች ጊዜያት በብዙ መልኩ ይለያል፡፡ በዓሉ የአንድነት ፅናታችን መተሳሰሪያና የህዳሴ ጉዞአችን ማረጋገጫ በሆነው በታላቁ የህዳሴ ግድብ ግንባታ መገኛ ክልል መከበሩ ከሁሉም በላይ ዕለቱን ልዩ አድርጎታል፡፡ የአፈፃፀም ክንውኑ ከ42 በመቶ በላይ በደረሰው በዚሁ በታላቁ የህዳሴ ግድብ መገኛ ስፍራ ጁባ የዋዜማ ዝግጅቱን የጀመረውና በአሶሳ ደምቆ የተጠናቀቀው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል ከመቼውም ጊዜ በበለጠ የሁሉንም ትኩረት ስቧል፡፡ ለዘመናት የዘለቀውን የአንድነት ፅናታችንንና የእድገት ግስጋሴያችንን ውጤታማነት ለዓለም ህብረተሰብ አጉልቶ አሳይቷል፡፡

መንግስት ከህዝቦቹ የተቀበለውን አገራዊ አደራ በመልካም አፈፃፀም እየመራ የህዳሴውን ጉዞ ምን ደረጃ ላይ እንዳደረሰው ለሁሉም ግልፅ አድርጓል፡፡ የህዝብ እንደራሴዎች የህዳሴውን ግንባታ ሂደት በተለያዩ የግንኙነት አግባቦች ከመስማት አልፈው በዓይናቸው እንዲያዩ ሰፊ እድል ፈጥሯል፡፡ ከዚያም ባለፈ የጋራ ቃልኪዳናቸውን እንዲያድሱ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ሆኗል፡፡ በይቻላል መንፈስ በቆራጥነት የተጀመረውን የእድገትና የሽግግር ሂደት በዘላቂነት ለማስቀጠል ያላቸውን ዝግጁነትም ለአደባባይ አብቅቷል፡፡

የሚናፈቀውን አገራዊ ለውጥ በሁለንተናዊ መልኩ በማረጋገጥ አዲሱን የታሪክ ምዕራፍ ወደላቀ ደረጃ ለማሸጋገር ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች ንቁ ተሳትፎ ይጠበቃል፡፡ ለውጥ በዋናነት የለውጥ ኃይሎችን አጥብቆ ይሻል፡፡ በዚህ ሂደት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ቀዳሚ ተሰላፊዎች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህን ኃይል ሳይዙና በዚህ ኃይል በአግባቡ ሳይጠቀሙ ፈጣን ዕድገትንና አገራዊ ተጠቃሚነትን ማሰብ ይከብዳል፡፡

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተማረ ሰው መፍለቂያ ከመሆናቸው አንጻር አገርን ለማልማትም ሆነ ለውጥን ለማምጣት ትልቅ አስተዋጽኦ አላቸው፡፡ ተቋማቱ ይህንን ሀላፊነት ለመወጣት በተሻለ ጥረትና በጋራ ተነሳሽነት የሀገራችንን ገፅታ ለመቀየር ዋነኛውን የለውጥ ኃይል በተገቢው መልኩ ከጎናቸው ማሰለፍ ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹን መልካም የግንኙነት መድረኮች በአግባቡ ተጠቅሞ የተማረው ኃይል አገራዊውን የአንድነትና የጋራ ተጠቃሚነት መንፈስ በእውቀትና በክህሎት እንዲመራውና እንዲያስተባብረው መልካም አጋጣሚዎችን መፍጠር የጉዳዩ ባለቤቶች ማለትም የተቋማቱ አመራሮች ድርሻ ይሆናል፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች አፍላ ጉልበታቸውንና በሳይንሳዊ መልኩ የተደራጀ እውቀታቸውን አቀናጅተው ሀገርንና ወገንን እንዲጠቅሙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት እንደሚያስፈልግ ይታመናል፡፡ በግንኙነት መድረኮቹ መነሻነት የውይይት፣ የምክክርና የግንዛቤ ማዳበሪያ ዝግጅቶችን ተከታታይነት ባለው መልኩ ማቅረብ እንደሚገባ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ያምናል፡፡ ይህንንም በተግባር እየፈጸመ ይገኛል፡፡ እንዲህ ያሉ አጋጣሚዎች የእውቀት ግብይት መድረኮች እንዲሆኑም ክንውኑን በእቅድ በመመራት ውጤታማ ሥራዎችን ማከናወኑን ይቀጥላል፡፡

ዩኒቨርሲቲው በሀገር ህልውናና ዘላቂ ጥቅም ላይ ወሳኝነት ባላቸው ብሄራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ጥናትና ምርምርን መሰረት ያደረጉ ርዕሰ ጉዳዮችን በመለየት መምከርና መዘከር እንዲሁም የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችም ሆኑ የተቋሙ ማህበረሰብ ድርሻ መሆኑን ተገንዝቦ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ የእውቀትና ክህሎት ባለቤት የሆኑት የተቋሙ ተማሪዎች ድርሻ እንደተባለው በሀገራዊው እድገትና በዜጎቿ ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት ዙሪያ ጉልህ ሚና እንዳለው ይገነዘባል፡፡ በመሆኑም የብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓልና ሌሎችም በአላትን ስናከብር ከበአልነት አልፈው በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተውን አንድነት በማጠናከርና የባህል ልውውጥ በማድረግ ዘላቂ እድገትንና የጋራ ተጠቃሚነትን ትርጉም ባለው መልኩ ለማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡ ስለዚህ አገራዊ ለውጥ ለማምጣት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች የጎላ አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ዩኒቨርሲቲያችን ድጋፉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል እናረጋግጣለን፡፡

## ቁልፍ መልዕክት

### የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በራዕይ ጥበብ 2017 ቅኝት መመራት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ምን አይነት መሠረተ ልማት ይኑረው? የሰው ኃይል ልማቱስ እንዴት መመራት ይችላል? ውስጣዊ የቤተ-ሙከራና የሆስፒታል የመመርመሪያ ዕቃዎች እንዴት ማሟላት ይቻላል? የሚሉትን መሠረታዊ ጥያቄዎች በማንሳት ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ በዚህም መሠረት ብዙ ነገሮች ግልጽ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ በተግባርም እየተፈፀሙ መሆናቸውን ስናይ ከፍተኛ ተስፋ ይሰጠናል፡፡ ይህ አጭር ጽሑፍ ስለህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጃችን በራዕይ ጥበብ 2017 ቅኝት ምን መልክ እንዲኖረው ታስቦ እየተሠራ እንደሆነ ለማጋራትና ከዚህም አንፃር ቀጣይነት ያለው ውይይቶችን የሚጋብዝ ሁኔታ ለመፍጠር አለማ አድርጎ ተነስቷል፡፡

ከህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ አንፃር የሚጠበቁ ወሳኝ ውጤቶችን በምናይበት ወቅት ማዳንና መከላከል ሁለት ቁልፍ ውጤቶች ሆነው እናገኛለን፡፡ ከማዳን አንፃር በተለያዩ በሽታዎች የታመሙ ዜጎችን በሆስፒታላችን ለህክምና ሲመጡ አክመን የማዳን አቅማችን እንዲሁም በእኛ የህክምና ትምህርት ያለፉ ሀኪሞችን በተለያዩ የሀገራችን የጤና ተቋማት ሲሰማሩና በሙያቸው አክመው የማዳንን አቅም ያካትታል፡፡ እነዚህን ሁለት የማዳን አቅሞች በሚገባ ለማዳበርና ለማሳካት ቁልፍ ጉዳይ የሚያስተምሩና ህክምና የሚሰጡ ሀኪሞቻችንን በስፔሻላይዜሽን በሰብ ስፔሻላይዜሽን ማሰልጠን ነው፡፡ በራዕይ ጥበብ 2017 የተያዘው አቅጣጫም ይኸው ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ይህን አቅጣጫ በተግባር ለመፈፀም ያለው ቁርጠኝነት ከፍተኛ ስለሆነ ሀኪሞቻችንም ይህን አቅጣጫ በመረዳት በሙያቸው ከፍተኛ ክህሎት ለመገንባት መነሳሳት ይኖርባቸዋል፡፡

ሆኖም ግን ሀኪሞች በሚገባ ሰልጥነው የሚሰሩበት መሳሪያ ከሌለ ማዳንም ሆነ የሚያድን ሀኪም አሰልጥነው ማውጣት ይከብዳቸዋል፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የህክምና ዕቃዎችን የማሟላት ጉዳይ በራዕይ ጥበብ 2017 ልዩ ትኩረት የሰጠው ሁለተኛው ጉዳይ ነው፡፡ በዚህም መሠረት ወገብ የሚያስጎብጥ አይነት ስራ እንደሚጠብቀንና መጠነ ሰፊ ወጭ እንዳለው ተገንዝበን ልንቀሳቀስ ይገባል፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ልናተኩርበት የሚገባ ጉዳይ ለተማሪዎችና ለሀኪሞች ተስማሚና ምቹ አካባቢ መፍጠር ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከመኖሪያ ቤት ጀምሮ በርካታ ስራዎች እየተሠሩ ነው፡፡ በአራተኛ ደረጃ አለማቀፋዊ ትብብሮችን በሚገባ ማስፋፋት ይመለከታል፡፡ የእኛ ሐኪሞችና ተማሪዎች በተለያዩ ሀገሮች እየሄዱ ልምድ መቅሰም ይገባቸዋል፡፡

ምንም ምንኳ ድንበር የሌለው ቢሆንም በሽታን መከላከልን በዋናነት እንዲሠራው የሚፈልገው የጤና ትምህርት ዘርፉ ነው፡፡ የሀገራችን ዜጎችን በብዛት መታደግ የሚቻለው መከላከል ላይ በሚገባ በመስራት ነው፡፡ ለዚህም ነው መንግስት መከላከልን መሠረት ያደረገ የጤና ፖሊሲ ያዘጋጀው፡፡ ለማዳን የሐኪሞቻችንን አቅም መገንባት ወሳኝ እንደሆነ ሁሉ ለመከላልም የጤና ባለሙያዎቻችን ግንባታ ወሳኝ ነው፡፡ በመሆኑም የራዕይ ጥበብ 2017 አቅጣጫ መሰረት በማድረግ የጤና ባለሙያዎቻችንን አቅም ለማሳደግ እስከ 3ኛ ዲግሪ ድረስ ትምህርት ለመስጠት ርብርብ እያደረግን ነው፡፡

የህብረተሰባችንን የጤና ችግሮች መለየትና መስራት ያለብንን ጉዳይ ማወቅ እንድንችል እንደመነሻ በሜጫ ወረዳ በተወሰኑ ወረዳዎች የሚኖረውን ህዝብ በሚገባ መዝግበን መከታተል የሚያስችለንን ስርዓት ለመገንባት እየሠራን ነው፡፡ በአካባቢያችን ያሉ የጤና ችግር የሚሆኑ ጉዳዮችን በሚገባ መለየት፣ መተንበይና የመከላከያ ዘዴዎችንም ለማህበረሰቡ ማስተማር ወሳኝ ናቸው፡፡ በመሆኑም ሁለገብ የጤና የመረጃ ስርዓት መገንባት ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ የመከላከል ስራዎች ላይ ትርጉም ያለው ሚና መጫወት የሚችሉ ሙያተኞች በጥራት ማፍራት የሚቻለውም በዚህ ሁኔታ በተግባር በማስተማር ነው፡፡

በአጠቃላይ በባሕር ዳር ፈለገ ህይወት ሆስፒታል ያለንን ግቢ በማስፋፋትና በማጠናከር እንዲሁም የጢስ አባይ ግቢያችንን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ በማጠናቀቅ ወደ ተለያዩ ቦታዎች የህክምና አገልግሎት ፍለጋ የሚሄዱትን ዜጎቻችንንና ይህንን ለመፈፀም አቅሙ ለሌላቸው ተደራሽ በመሆን የማህበረሰባችን መመኪያና አለኝታ ኮሌጅ ለመመስረት በራዕይ ጥበብ 2017 የተቀመጠውን የኮሌጃችንን አቅጣጫዎች ለመተግበር እንረባረብ፡፡

**ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!!!**

# አበይት ዜናዎች...

## አገር አቀፍ የመሬት ምርምርና ልማት ትስስር ተመሰረተ

ሙሉጎጃም አንዷለም

ባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ አስተባባሪነት አገር አቀፍ የመሬት ምርምርና ልማት ትስስር (ኢትዮላንድኔት) በይፋ ተመሰረተ፡፡ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ አውደ ጥናቱን ሲከፍቱ በቅድሚያ ለትብብሩ ድጋፍ ያደረጉ አካላትን በማመስገን የምርምር ትስስሩ በኢትዮጵያ የመሬት ጉዳዮች ዙሪያ ለሚደረጉ የምርምር ሥራዎች ለልማት በሚውሉበት አቅጣጫ ላይ የሚያተኩሩ ስለሆነ ለሀገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ያለው ሚና ወሳኝ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ትስስሩ መረጃ በመሰብሰብ ፖሊሲዎችን ለመቅረጽ ግብአት ስለሚሆኑ ዩኒቨርሲቲው ድጋፍ እንደሚያደርግ ተናግረዋል፡፡

የአሜሪካ ዓለም አቀፍ ልማት ኤጀንሲ ተጠባባቂ ዳይሬክተር ጌሪ ሊንደን የትስስር መረቡ የመሬት አስተዳደርን በማሳለጥ ረገድ ስለሚኖረው ጠቀሜታ ሲገልጹ የምርምሩ ስኬት በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ላይ ከተቀመጡ ግቦች ጋር ተያያዥነት ባለው መልኩ ለመሬት ልማት የፖሊሲ ቀረፃና የምርምር ውጤቶች አጋዥ መሆን እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ መሬት አስተዳደር ተቋም ዳይሬክተር ዶ/ር ታደሰ አምሳሉ የምርምር ትስስሩ መቋቋም ዋና ዓላማ ከመሬት መጠቀም የሚገባንን በቂ የሆነ የመስክ መረጃ መሰብሰብና ምርምሩ በመሬት ዙሪያ የሚደረጉ ጥናቶች ለውይይት የሚቀርቡበትና ታትመው የሚሰራጩበትን መድረክ ለማመቻቸት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው በበኩላቸው እንደተናገሩት የተቋቋመው የምርምር ትስስር ሀገራዊ ኩራትን የሚያጎናጽፍ ስለሆነ በውይይቱ ወቅት የተነሱትን ሃሳቦች ወደ ተግባር መለወጥ እንደሚገባና ሥራው መጠናከር እንዳለበት ገልፀዋል፡፡ በመሬት ዙሪያ ያለውን ችግር ለመፍታትና ለማህበረሰቡ በተጨባጭ ለማድረስ ሁሉም የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ተናግረዋል፡፡

የምርምር ትስስሩ በመሬት ዙሪያ የሚሠሩ ምርምሮችን የሚያስተዋውቅና ግኝቶችን የሚያሰራጭ ሲሆን በአብዛኛው በመሬት ዙሪያ ለሚደረገው እንቅስቃሴ በገጠርና በከተማ ህዝብ ላይ በዘርፉ የሚደረጉ ምርምሮችና የሚሰበሰቡ መረጃዎች በትክክል ስራ ላይ መዋል እንደሚገባቸው ጠቋሚ አካል እንደሆነ ታውቋል፡፡ ትስስሩ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ፣ ሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ፣ መቀሌ ዩኒቨርሲቲ፣ አዲስ አባባ ዩኒቨርስቲ፣ የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር፣ የማህበራዊ ጥናት መድረክ፣ የኢፌዲሪ የግብርና ሚኒስቴር እና የኢፌዲሪ የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ሚኒስቴር የተመሰረተ ነው፡፡

## የስራ ፈጠራ ስልጠና ተሰጠ

ታድዬ አስማረ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ካስኬፕ ፕሮጀክት በደቡብ አቸፈር ወረዳ ዱርቤቴ ከተማ ለሚገኙ ሴቶች ሥራ ፈጥረው በኢኮኖሚ ተጠቃሚ የሚያደርግ የምግብ አዘገጃጀት ስልጠና ሰጠ፡፡ ስልጠናው ሴቶች በአካባቢያቸው በቀላሉ ከሚገኙ የምግብ አይነቶች በመጠቀም ምግብ እንዴት ማዘጋጀት እንደሚችሉና በፋብሪካ ውስጥ የሚመረቱ ምግቦችን በቤት ውስጥ መስራት እንዲችሉ ለማሳየት ታስቦ የተዘጋጀ ነው፡፡

የካስኬፕ የስነ-ምግብ ተመራማሪ አቶ አቤል አህመድ እንደገለጹት በአካባቢው በሚገኙ የምግብ ዓይነቶች ላይ ስልጠናው ማተኮሩ ሴቶች በአነስተኛ የኢኮኖሚ መነሻ መጀመር እንዲችሉ የሚያስችላቸውና በፋብሪካ እየተመረቱ ለገበያ በሚቀርቡ የፋብሪካ ውጤቶችን መሰረት በማድረግ ምግብ ማዘጋጀትና ከሁለት ሳምንት እስከ ስድስት ወር ሳይበላሽ እንዲቆይ ማድረግ የሚያስችላቸው ስልጠና እንደሆን ገልጸዋል፡፡ ስልጠናው ሰልጣኞቹ በኢኮኖሚ ተጠቃሚ ከማድረግ በተጨማሪ በምግብ አዘገጃጀት ወቅት ሊደረጉ የሚገባ ጥንቃቄዎችን በመተግበር ጤናማ ማህበረሰብ እንዲፈጥሩ በማድረግና የአካባቢው የአመጋገብ ስርአት እንዲሻሻል በማድረግ ትልቅ አቅም እንደሚፈጥርላቸው ተናግረዋል፡፡

የካስኬፕ ፕሮጀክት የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት የማህበረሰብ አገልግሎት በሚሰጥባቸው የተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በመስጠት እንዲሁም በኢትዮጵያ ውስጥ መንግስት የግብርና ዘርፉን ለማሳደግ እያደረገ ያለውን ጥረት በመደገፍ ሀገር በቀል እውቀቶችን ወደ ሳይንሳዊ ምርምር በመውሰድ የተሻሻለ የግብርና አሠራር እንዲኖር እየሰራ የሚገኝ ፕሮጀክት ነው፡፡

## የገጠር ሞዴል ከተማ ተመሠረተ

የማነ ገብሩ

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በደቡብ ጎንደር ዞን ሊቦ ከምከም ወረዳ የቡራኔስት ሁሉን አቀፍ የገጠር ሞዴል ከተማ ምሥረታ ላይ የሚመክር አውደ ጥናት አካሄደ፡፡ በፕሮጀክቱ ትግበራ ላይ የተገኙ ውስንነቶችንና ጠቃሚ ተሞክሮዎችን ለይቶ በማደራጀት በቀጣይ አርሶ አደሩን ያለምንም ችግር በገጠር ከተማ እንዲከትም ፍኖተ ካርታ ማዘጋጀት ላይ ያተኮረ አውደ ጥናት ነው፡፡

የዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው በዐውደ ጥናቱ ላይ እንደተናገሩት አርሶ አደሩ የኑሮው መሠረት የሆነው ግብርናን ሳይለቅ ዘመናዊ የገጠር ከተማ እንዲመሠረት፤ ማህበረሰቡም በዕውቀትና በክህሎት ላይ የተመሠረተ የኑሮ ዘዴ እንዲከተል ለዚህ ተግባራዊነት ደግሞ ዩኒቨርሲቲው አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ ያደርጋል ብለዋል፡፡

በገጠር አርሶ አደሩ በዘመናዊ ከተሞች እንዲከትም በማድረግ ሁሉን አቀፍ የልማት ተጠቃሚ ለማድረግና እና የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታስቦ እንጂ ነጠላ የመንደር ምስረታ እንዳልሆነ የገለፁት የNew Ethiopian Sustainable Town (NEST) Group ፕሬዚዳንት ፕሮፌሰር ፍራንስ አስዋልድ ናቸው፡፡ በአርሶ አደሩ ሙሉ ፍቃደኝነትና ተሳትፎ በአንድ አካባቢ መከተም ከተቻለ የህብረተሰቡ ማህበራዊ ግንኙነት ከማጠናከር በተጨማሪ በመንግስት የሚከናወነውን የመሰረተ ልማት ማስፋፍያ እና ማህበራዊ አገልግሎት ግንባታ ላይ በቀላል ወጭ፣ በአጭር ጊዜ እና በፍጥነት ተጠቃሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎን አርሶ አደሮች ግብርናን በዘመናዊና በተቀናጀ ሁኔታ በማስፋፋት ምርታማ እንዲሆኑና በእውቀትና ክህሎት ላይ የተመሠረተ አመራረት እንዲከተሉ ይረዳል ብለዋል፡፡

በአውደ ጥናቱ መዝጊያ ሥነ-ስርአት ላይ የተገኙት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ የቡራኔስት ገጠር ከተማ ምስረታ እንደ ቤተ-ሙከራ በመውሰድ ፕሮጀክቱ ወደ ሌሎች ወረዳዎች ከመስፋፋቱ በፊት መሠረታዊ ጥናት ተደርጎበት ዘላቂነት ያለውና የህብረተሰቡን ፍላጎት የሚመልስ መሆን እንዳለበት መልእክት አስተላልፈዋል፡፡

## የብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ቀን ተከበረ

አበባ ሐብቱ

9ኛው የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በዓል በደመቀ ሁኔታ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስታድየም ተከብሯል፡፡ በዓሉ በዩኒቨርሲቲው ኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሙኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት አዘጋጅነት "በህገ መንግስታችን የደመቀ ኢትዮጵያዊነታችን ለህዳሴያችን" በሚል መሪ ቃል የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች በተገኙበት በተለያዩ ዝግጅቶች ተከብሯል፡፡

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደር ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር እያዩ ሞላ በዓሉ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተውን አንድነት በማጠናከር የባህል ልውውጥ ለማድረግ ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በትምህርት ልማት ሠራዊት ግንባታ አቅጣጫ በመመራት የኢትዮጵያን ህዳሴ ለማፋጠን የተጀመረውን ዘርፈ ብዙ ጥረት በማጠናከር ታሪካዊ አሻራውን ለማኖር በትጋት መሥራት እንደሚኖርበት ዶ/ር እያዩ አሳስበዋል፡፡

በእለቱ የቀረቡ የተለያዩ ባህላዊ ሙዚቃዎች፣ ድራማ እና ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦችን የሚያስተዋውቁ የአልባሳትና ባህላዊ ጭፈራዎች ለበዓሉ ድምቀት ሰጥተውታል፡፡

## የኤች አይ.ቪ. ኤድስ ቀን ተከበረ

አበባ ሐብቱ

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ "አንድም ሰው በኤች አይ ቪ እንዳይያዝ፣ እንዳይገለል፣ እንዳይሞት፣ ሃላፊነታችንን እንወጣለን" በሚል መሪ ቃል የኤች አይ ቪ ኤድስ ቀን ተከበረ፡፡ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጤንነቱ የተጠበቀ ስኬታማ ትውልድ ከመቅረጽ አንጻር ጉልህ ሚና እንዳላቸው ተጠቅሷል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዳይሬክቶሬት አዘጋጅነት በተከበረው በዓል ላይ ንግግር ያደረጉት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት ሃላፊ አቶ ምህረቴ ዋለ ዕለቱ በኤች አይ ቪ ኤድስ ጉዳዮች ዙሪያ የተገኙ መልካም ውጤቶችን የምናስቀጥልበትና ቃላችንን የምናድስበት ነው ብለዋል፡፡ የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ሲስተር ማርታ አስማረ በበኩላቸው በዩኒቨርሲቲዎች፣ በኮሌጆች እና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ወጣቶች ከፍተኛ ለቫይረሱ የተጋላጭነት ባህሪያት እንደሚታይባቸው ጠቅሰው የዩኒቨርሲቲ የኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ዳይሬክቶሬት ለተማሪዎች እና ኤች አይ ቪ በደማቸው ላለባቸው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ትኩረት በመስጠት የተለያዩ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ ተናግረዋል፡፡

ሴቶች በኤች አይ ቪ ኤድስ የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍተኛ መሆኑን ጥናቶች እንደሚጠቁሙ የገለፁት የፔዳጐጂካልና የስነ-ትምህርት ምርምር ተቋም ዳይሬክተር ዶ/ር ረዳ ዳርጌ እየተሰራ ያለው ግንዛቤ የመፍጠር ስራ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አስገንዝበዋል፡፡ በዕለቱ በዓሉን በማስመልከት በተካሄደው የእግር ኳስ ውድድር የዩንቨርሲቲው ኤች አይ ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠሪያ ዳይሬክቶሬት የስነ- ምግባርና ፀረ-ሙስና ዳይሬክቶሬትን 4 ለ 3 በሆነ ውጤት ማሸነፉ ታውቋል፡፡ በአሉ ህዳር 22 በሀገር አቀፍ ደረጃ ለ26ኛ ጊዜ ተከብሮ እንደሚውል ታውቋል፡፡

# አበይት ዜናዎች...

## በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር አዲስ የቪዛ አገልግሎት ይፋ አደረጉ

### • አምባሳደሯ አካዳሚውን ጎበኙተዋል

**አምሳሉ ጥላሁን**

በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር ፓትሪሽያ ሀስላክ ለባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ማሪታይም አካዳሚ ምህንድስና ምሩቃን አዲስ የቪዛ አገልግሎት ይፋ አደረጉ፡፡ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ በእለቱ እንደገለጹት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ዩኒቨርሲቲው በ2017 ዓ.ም. አፍሪካ ውስጥ ከሚገኙ አስር የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን ያለውን ራዕይ ለማሳካት አስራ አንድ የምርምር ማዕከላትን አቋቁሞ እየሠራ እንደሚገኝ እንዲሁም ዩኒቨርሲቲው መንግስታዊምና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት ጋር አዲሲቷን ኢትዮጵያ ለመገንባት እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

አምባሳደር ፓትሪሽያን በበኩላቸው አሜሪካ በባሕር ጉዞ ትልቅ ልምድ ያላት አገር እንደሆነች ጠቅሰው የኢትዮጵያ ማሪታይም አካዳሚ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከYCF ከሚባል የአሜሪካ ኩባንያ ጋር በትብብር የተመረሰተ ሲሆን በአለም አቀፍ ደረጃ ውጤታማ የባህር ላይ አገልግሎት እየሰጠ የሚገኝ ድርጅት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ኢትዮጵያ በውሃ ላይ ምህንድስና በሙያቸው ብቃት ያላቸው ባለሙያዎች እንዳሏት የተናገሩት አምባሳደሯ የአሜሪካ መንግስት ይህን በመረዳት ለኢትዮጵያ የባህር ላይ ምህንድስና ምሩቃን ወደ አሜሪካ ለመግባትና ለመውጣት የሚያስላቸውን አዲስ የቪዛ አገልግሎት እንደሚጀምር ተናግረዋል፡፡ አምባሳደሯ አካዳሚውን ጎበኙተዋል፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የማሪታይም አካዳሚ የአራት ዓመት ዕድሜ ያለው እንደሆነና በአጭር ጊዜ ውስጥ ከ850 በላይ የባሕር ምህንድስና ባላሙያዎችን ያፈራ መሆኑን የገለጹት የኢትዮጵያ የማሪታይም አካዳሚ ዋና ስራ አስኪያጅ ጆርደን ቡችለር ዩኒቨርሲቲው በባሕር ላይ ምህንድስና በቂ ዕውቀት፣ በስነ-ምግባራቸው የተመሰገኑ፣ ችግርን መቋቋም የሚችሉ ባለሙያዎችን በማፍራት ለሀገሪቱ ትልቅ አስተዋጽኦ እያበረከቱ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ አምባሳደሯ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የብሉ ናይል ውሃ ኢንስቲትዩት ባዘጋጀው አውደ ጥናት ላይ ባደረጉት ንግግር የአሜሪካ መንግስት ችግር ፈች ምርምር የሚያደርጉ አካላትን እንደሚያግዝ ተናግረዋል፡፡

## የህግ ትምህርት ቤት ስልጠና ሰጠ

**አምሳሉ ጥላሁን**

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ህግ ትምህርት ቤት የግልግል ዳኝነት ማዕከል ‹‹የገላጋዮች›› ስልጠና ሰጠ፡፡ በስልጠናው ላይ የተገኙት የህግ ትምህርት ቤት ዳይሬክተር ዶ/ር ሚዛኔ አባተ በአሁኑ ወቅት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በመማር ማስተማር፣ በምርምርና በማህበረሰብ አገልግሎት ላይ ትኩረት በመስጠቱ የህግ ትምህርት ቤቱም የዮኒቨርሲቲውን ተልዕኮዎች ለማሳካት እየሠራ እንደሚገኝና ይህ ስልጠናም አንዱ የማህበረሰብ አገልግሎት አካል እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ የህግ ትምህርት ቤት በየዓመቱ በክልሉ ውስጥ ላሉ ባለሙያዎችና ሐላፊዎች እንደዚህ ያሉ ስልጠናዎችን በማዘጋጀት እየሰጠ እንደሚገኝ እና ነፃ የህግ አገልግሎት በተማሪዎችና በመምህራን በባሕር ዳር ከተማ እና በባሕር ዳር ዙሪያ እንዲሁም በአጎራባች ዞኖች ላይ የማህበረሰብ አገልግሎት እየሰጠ እንደሆነ፤ ወደፊትም በማህበረሰቡ ላይ ያሉትን ችግሮች ለመቅረፍ ትምህርት ቤቱ ጠንክሮ እንደሚሠራ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ገልጸዋል፡፡

ዘመናዊ የህግ ዳኝነት ከመምጣቱ በፊት በዋናነት ሲያገለግል የነበረው የግልግል ዳኝነት እንደነበረና በአሁኑ ወቅት በገጠራማው የሀገራችን ክፍል እያገለገለ እንደሚገኝ፤ ለማህበራዊ፣ ለኢኮኖሚያዊ፣ ለፖለቲካዊ ሁነቶችም ትልቅ አስተዋጽኦ ሲያደርግ የቆየና አሁንም የራሱን ሚና እየተጫወተ እንደሚገኝ የገለጹት በአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር በምክትል ርዕሰ መስተዳድር ማዕረግ የርዕሰ መስተዳድሩ የህግ አማካሪ አቶ መርሐጽድቅ መኮንን ናቸው፡፡ የባህላዊ የግልግል ዳኝነት ባለፉት ዘመናትም ሆነ በአሁኑ ወቅት ለማህበረሰቡ ትልቅ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት ቤት ለባለሙያዎች የሚሰጠው ስልጠና የበለጠ ግንዛቤ የሚፈጥር ስለሆነ ስልጠናው በጣም አስፈላጊ እንደሆነ ወደፊትም የበለጠ አጠናክረው እንዲሠሩ አሳስበዋል፡፡

በስልጠናው ላይ የአማራጭ የክርክር መፍቻ ስልት፣ ህገ-መንግታዊ መሰረት በኢትዮጵያ፣ የአማራጭ የክርክር መፍቻ ስርዓት አዎንታዊና አሉታዊ ጎኖች፣ ልማዳዊ አሰራርና አማራጭ የክርክር መፍቻ ስልት፣ ባህላዊና ዘመናዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ተመሳሳይነትና ልዩነት፣ የድርድር ስልቶች፣ ለስኬታማ የድርድር ሂደት አስፈላጊ የሆኑ ክህሎቶች፣ የድርድር ስምምነት ህጋዊ ውጤት፣ ማግባባት፣ ዕርቅ እና የግልግል ዳኝነት የሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች የስልጠናው ተግባራት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## ለሴት መምህራን ስልጠና ተሰጠ

**አምሳሉ ጥላሁን**

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ከትምህርት ሚኒስቴር እና ሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር ‹‹የኢትዮጵያ ሴቶች ትግል እና የህዳሴ ጉዞ›› በሚል ርዕስ ለሴት መምህራን ለሁለት ቀን በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስልጠና ሰጡ፡፡

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ ጉዳዮች ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ማተቤ ታፈረ መንግስት ለትምህርት ትኩረት በመስጠት ዩኒቨርሲቲዎችን በማስፋፋት ላይ እንደሚገኝ ጠቁመው በአሁኑ ወቅት የትምህርትን ተደራሽነትንና ጥራትን ከማረጋገጥ አንፃር እየሠራ እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም በአሁኑ ወቅት የትምህርት ጥራትን ለማረጋገጥ፣ ሴቶችን ወደ አመራር ለማምጣት እንዲሁም ሴት ተማሪዎችን ለማብቃት እየሠራ እንደሚገኝ በመጠቆም ይህንንም ወደ ተግባር በመቀየር በ2006 ዓ.ም የተለየ ዕድል በማመቻቸት ከየትምህርት ክፍሉ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ሴት ተማሪዎችን እንደቀጠረ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል፡፡

የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር የተከበሩ ወ/ሮ ዘነቡ ታደሰ በ2017 መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች ተርታ ለመድረስ ዕቅድ ይዞ መንግስት እየሠራ እንደሚገኝና ሴቶች ለዚህ ራዕይ መሣካት የራሳቸውን ሚና መጫወት እንደሚችሉ በተለይ ዩኒቨርሲቲዎች በሰው ልጅ አዕምሮ ልማት ላይ የሚሠሩ ተቋማት በመሆናቸው ለሀገር ዕድገት ትልቅ አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡

በስልጠናው ወቅት የኢትዮጵያ ሴቶች ትግል እና የህዳሴ ጉዞ ገጽታዎች፣ የአገራችን ሴቶች የቅድመ አብዮት ጭቆና ገጽታዎች፣ የሴቶች የጸረ ጭቆና ትግል፣ የኢፌዴሪ ህገመንግስት ታሪካዊ ቦታ ከሴቶች አኳያ፣ ህገ መንግስታዊ ትሩፋቶች፣ ተግዳሮቶች እና የዩኒቨርሲቲ ሴት ተማሪዎችን ማብቃት በሚቻልባቸው ሁኔታዎች ዙሪያ የመነሻ ፅሑፎች ቀርበው ውይይት ተካሂዶባቸዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች የዕውቀት ማማ በመሆናቸው ለሴት መምህራንና ተማሪዎች የድጋፍና የክትትል መርሐ ግብር አስቀምጦ ሊሠሩ እንደሚገባቸው በተለይም ሴት መምህራና ድጋፍ ሰጭ ሴት ሠራተኞች ወደ ከፍተኛ አመራርነት እንዲመጡ ዩኒቨርሲቲዎች የራሳቸውን አስተዋጽኦ ሊያደርጉ እንደሚገባው በስልጠናው ላይ አፅንኦት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ በስልጠናው ላይ ከባሕር ዳር፣ ከጎንደር፣ ከደብረማርቆስና ከደብረታቦር ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ሴት መምህራን፣ የስርዓተ ፆታ ዳይሬክተሮችና የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንቶች ተሳትፈዋል፡፡

## የአካባቢ ጥበቃ ቀን ተከበረ

**ትዕግስት ዳዊት**

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ኘሬዝዳንት ጽ/ቤት የአካባቢ ጥበቃ ቀንን የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ፣ ከግልና ከመንግስት መስሪያ ቤቶች ከመጡ ተወካዮች እንዲሁም ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ ምሁራን በተገኙበት አከበረ፡፡

የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ምክትል ፕሬዚዳንት ዶ/ር ተስፋዬ ሽፈራው ህዳር 5 ቀን የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ከባሕር ዳር ከተማ ነዋሪዎች ጋር በመተባበር የአካባቢ ጥበቃ እና የፅዳት ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማሠብ ቀኑ እንደሚከበር ገልፀዋል፡፡
በዕለቱ ከባሕር ዳር አካባቢ ተቆርቋሪዎች ማህበር፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጡ ተጋባዥ እንግዶችና በዘርፉ ጥናት ያደረጉ ተመራማሪዎች የአካባቢ ጥበቃ እና ተዛማጅ የሆኑ ጉዳዮች ላይ የምርምር ውጤታቸውን አቅርበዋል፡፡ የምርምር ውጤታቸውን ካቀረቡት መካከል አንዱ ዶ/ር ብርሃኑ ገ/ማርያም በየቁራው የሚጠራቀመውን ደም በማድረቅ እና በመፍጨት ለእንሰሳት መኖ እንዲሁም ለማዳበሪያነት እንዲውል የሚያደርገውን ቴክኖሎጂያቸውን በማስተዋወቅ ቴክኖሎጂው አካባቢን ከብክለት እንደሚከላከል ገልፀዋል፡፡

በቅርቡ በጣና ሀይቅ ላይ የተከሠተውን አረም በተመለከተ ጥናት ያደረጉት ዶ/ር ዋሴ አንተነህ ጣና የህብረተሰቡ ህልውና በመሆኑ ጣናን መጠበቅ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡ በጣና ላይ የተከሠተው አረም መምጫው እስከሁን እንዳልታወቀ እና አረሙን ለማጥፋት በባለሙያዎች ርብርብ እየተደረገ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ዶ/ር ዋሴ አያይዘውም የደንገልን ተክል በጣና በሰፊው በመትከል የተከሠተው አረም መቀነስ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል፡፡

በቀረቡት ጥናቶች ላይ ከምሁራንና ከተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎች የተነሱ ሲሆን መልስ ተሠጥቶባቸው ውይይቱ ተጠናቋል፡፡

ዜናዎቻችንን በድረ-ገጻችን http://www.bdu.edu.et እና በፌስቡክ ገጻችን www.facebook.com/bduethiopia መከታተል ይችላሉ፡፡

# የዩኒቨርሲቲው ተማሪ ማስታወሻ

(ከጥቅምት ወር ዕትም የቀጠለ)

በፈታሒ በቃሉ

ሣጅን በመጠኑ ራቅ ብሎ ከወዲያ ወዲህ እያለ ሲጠብቀኝ ቆዬና አነጋግሬ ስጨርስ መጣና እሺ! በመቀጥል ደግሞ ለሔርሜላ መደወል አትፈልግም እንዴ! አለኝ፡፡ እኔም እሷ እንኳን ሰሞኑን ፈተና ስለሚኖራት ከቅዳሜ በኋላ ነፃ ስትሆን ብደውልላት ይሻላል፣ ስለው በነገሩ ተስማማና ወደ መኝታ ቤት አመራን፡፡ መኝታ ቤት እንደገባን የተሰጠውን አሳይሜንት ለመሥራት ጥያቄዎችን ተቀበልሁ፡፡ ለማጣቀሻ የተሰጡትን መጽሐፍት ለማግኘት የግድ መታወቂያ ስለሚያስፈልግ ወደ ላይበራሪ ከመሄዴ በፊት ሣጅንን ወሰድሁና መታወቂያውን አስይዞ ተቀበለልኝ፡፡ ከዚያም የማጣቀሻ መጻሕፍትን እያነበብሁ መሥራት ስጀምር ከተጠየቀው ጥያቄ ጋር ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት በማደርገው አሰሣ አዕምሮዬ ስለተሰባሰበልኝ የሆነ ሞራል ነገር ተሰማኝ፡፡

አሣይመንቱን በተመለከተ ለጥያቄዎች ተገቢ ማብራሪያ በመስጠጥ ብዙ ገጾችን መጻፍ ቻልሁ፡፡ ጥያቄዎችን ሠርቼ እንዳበቃሁ፣ የግድግዳውን ሰዓት ስመለከት ከምሽቱ አራት ሰዓት ተኩል በላይ ሆኗል፡፡ ሳስታውስ እራት አልበላሁም፡፡ በቃ ወደ ምኝታ ቤት ልሂድና በሶዬን አዘጋጅቼ ልጠጣ ብዬ ስሄድ ማንም ሰው የለም፡፡ ሁሉም ወደ ጥናት ሄደዋል፡፡

ራቴን ስላልበላሁ የበሶ ዱቄቴን በባለ ክዳኑ የበሶ መበጥበጫ ኩበያ ከውኃ ጋር ቀላቅዬ በመበጥበጥ ስቀምሰው ሊጥ፣ ሊጥ አለኝ፡፡ ሳስታውስ ለካንስ ስኳር አልጨመርሁበትም፡፡ ወዲያው በቂ ያህል ስኳር በመጨመር እንደገና በጠበጥሁና ስቀምሰው ይጣፍጣል፡፡ እሱን ግጥም አድርጌ ከጠጣሁ በኋላ ከደረቁ ዳቦ ቆሎዬ ዘግኜ በመያዝ እየቆረጠምሁ በግቢው ውስጥ እየተንዝሁ፣ ዛሬ የሠራሁት ሥራ ደስ ስላለኝ አዕምሮዬን ለማሰባሰብ እንድችል ምናለ አስተማሪዎች ሁል ጊዜ አሳይሜንት ቢሰጡ፣ በእውነቱ ዛሬ ያነበብሁትን መቼውንም አልረሳውም፡፡ በማለት በሩቁ ስመለከት ሦስት ሴቶች ከላይበራሪ በመውጣት ወደ ኦዲተሪየሙ አቅጣጫ ሲመጡ አየሁና ከሩቅ በመብራቱ ሳያቸው ቆይቼ ከመብራቱ እልፍ እንዳሉ፣ ጨለም ወዳለው አካባቢ ሲደርሱ ጠፉኝ፡፡ እኔም የሆነ ጥርጣሬ ነገር ተሰማኝና ከፊት ለፊት ወደ ኦዲተሪየሙ በመጠጋት ወደ ሱቁ በሚወስደው ማዕዘን ላይ ቆሜ ስከታተላቸው እያወሩ መጡ፡፡ ማመን አልቻልሁም፡፡ እሷም አብራ አለች፡፡ ህሴናዬ መፍራት ጉልበቴ መራድ ጀመረ፡፡ ልጥራት ወይንስ ወዴት እንደሚሄዱ ልከታተላቸው በማለት ኃሳቤ ከሁለት ተከፈለብኝ፡፡ ዝግ ብዬ እየተከተልሁ ሳዳምጣቸው የሚያወሩት ስለ አለፈው ሴሚስተር ውጤታቸውና ስለ መጭው ፈተና ነው፡፡ ትንሽ ሄዱና ሲቆሙ ቶሎ ብዬ በመብራቱ ብርሃን እንዳያዩኝ ዘወር በማለት ጨለም ወዳለው በኩል ቆሜ ስከታተል፣ አንደኛዋ ልጅ ከሌላዋ ልጅ ብር ተቀበለች፡፡ ወዲያው ፈጠን፣ ፈጠን እያለች መጣችና ወደ ሱቅ በመሄድ ባለሁለት ሊትሩን የታሸገ ውኃና ሦስት ፓኬት ብስኩቶች ገዛችና ዝግ ብላ እየተራመደች ሄዳ ከእነ ሔርሜላ ጋር ተቀላቀለች፡፡

እኔም በቅርብ ርቀት እየተከታተልኳቸው እያለ ትንሽ ከተራመዱ በኋላ ወደ ቀኝ በመታጠፍ በተለምዶ ተፉጠጥ ተብሎ ወደ ሚጠራው የሴቶች መኝታ ቤት ሕንፃ ውስጥ ገቡ፡፡ እኔ ግን ባለሁበት ቆምሁ ምክንያቱም ወንዶችወደ ሴቶች መኝታ ቤት አይደለም አብሮ መግባት ለመጠጋትም የተከለከለ ስለሆነ በሩቁ እየተመለከትሁ ሸኜኋቸው፡፡

> ወይኔ! ቶኪቻው ያኔ ወደ ከተማ ስሄድ ምናለ የምግብ ካርዴን እንኳን ትቸው ብሄድ ኖሮ በማለት መናደድ ጀመርሁ፡፡ ደግሞ ገንዘቡስ ቢሆን ቀላል ነው? ያች ምስኪን እናቴ በሬዋን ሸጣ አምስት መቶ አምሳ ብር…

ከሄዱ በኋላ ለምን ጠርቼ አላናግራትም ነበር፡፡ በማለት ወደ ኋላ ማሰብ ያዝሁና መልሼ አይ! ግዴለም እንኳን አድራሻዋን አወቅሁ እንጅ አላጣትም፡፡ ደግሞ ከነገ በኋላ ሻሼ ሞባይሏን ስለምትሰጠኝ ደውዬ አገኛታለሁ፡፡ በእርግጥ እሷ ከቅዳሜ በኋላ ተደዋውለን እንገናኛለን ብላለች፡፡ ነገር ግን እንዴት ሆኜ እስከዚያው መቆየት እችላለሁ፡፡ ባይሆን የደረሰብኝን ዝርፊያ እነግራትና ምን እንደምትል እሰማታለሁ፡፡ መቼም የምታዝን ይመስለኛል፤ ባለፈውስ ስላዘነች አይደል አፈላልጋ የሰጠችኝ፡፡ ደግሞ እኮ ስትሰጠኝ እንደገና ለማውጣት ያለውን ጣጣ ነግራኝ ነበር፡፡ ወይኔ! ቶኪቻው ያኔ ወደ ከተማ ስሄድ ምናለ የምግብ ካርዴን እንኳን ትቸው ብሄድ ኖሮ በማለት መናደድ ጀመርሁ፡፡ ደግሞ ገንዘቡስ ቢሆን ቀላል ነው? ያች ምስኪን እናቴ በሬዋን ሸጣ አምስት መቶ አምሳ ብር፣ ወደ ዩኒቨርሲቲ በመግባቴ የተደሰቱት አያቴ እና ሁለቱ አጎቶቼ መቶ፣ መቶ ብር ሰጥተውኝ በድምሩ ከአንድ ሺ ብር ያላነሰ ብር ይዤ ወደ ባሕር ዳር ገባሁ፡፡ ከዚያ ወዲህ ደግሞ አስተማሪዬና አጎቴ በድምሩ አንድ መቶ አምሳ ብር ሰጥተውኛል፡፡ በእርግጥ ከተሰረቅሁት ውጭ ያለውን ገንዘብ ያለ ምክንያት አላጠፋሁትም፡፡ የተጠቀምሁበት ለተገቢው ተግባር ብቻ ነበር፡፡ ‹‹የገንዘብ ምን ሥር አለው›› የምትለው አያቴ ልክ ናት፡፡›› ምናለ ተጠቅሜበት ቢጠፋ ኖሮ፡፡

እኔስ ያኔ ብሉ-በርድ ካፌ ላይ በተሰበሩት ነገሮች የከፈልሁትን ገንዘብ በተመለከተ ፈጣሪዬን አስቀይሜው ይሆን? ይህንን ተጨማሪ መዓት ያዘዘብኝ፡፡ በማለት ሳስብ ቆየሁና በቀጥታ ወደ ምኝታ ቤት ስሄድ የተወሰኑት ለመተኛት እየተዘጋጁ ነው፡፡ እኔ ስገባ መቀለድ የሚወደው ጓደኛችን ‹‹ጎጄ ደህና መጣህ? እኔስ ሌባህን ለማደን ትጥቅ ይዘህ የዘመትህ መስሎኝ ነበር፡፡›› እኛ ባለፈው በያዝኸው ሌባ የተነሣ፣ አንተ ካለህ ማንም አይነካን እያልን ስንኩራራ ለራስህም ሳትሆን ስትቀር ቀድሞውንም የሕክምና ተማሪ ብሎ ሌባ አዳኝ በማለት ነገሩን ትተነዋል፡፡›› አለና ንግግሩን ሲጨርስ ሁሉም ሣቁለት፡፡ እኔም ተው ትደርሳለች፡፡ በማለት አብሬ እስቅ ጀመር፡፡

ሰዓቱ እየመሸ ስለሄደ ሁላችንም አልጋችን ውስጥ እየገባን ተኛን፡፡ እኔም ቀን በጣም ደክሞኝ ስለዋለ ወዲያው እንቅልፍ ወሰደኝ፡፡ ተኝቼ እንደቆዬሁ በህልሜ ይመስለኛል አንዲት ሚዳቋ ወደ እኔ ስትመጣ አገኘትና ልይዛት ስከተላት ትንሽ እንደመሮጥ ትልና ቆም ብላ ወደ እኔ ስትመለከት፣ አሁንም ያለ የሌለ ኃይሌን አሰባስቤ ተከትያት ስሮጥ፣ በጎን በኩል ትልቅ ነብር ይመጣና አፉን ከፍቶ ወደ እኔ እየተመለከተ ሣዬው ከአሁን አሁን ዘሎ ያዘኝ በማለት እየተንቀጠቀጥሁ ከቆምሁበት ወደ ኋላ ለመሸሽ ስሞክር እግሬ ተተክሎ እምቢ ሲለኝ በፍርሃት ተውጬ የድረሱልኝ ጩኸት ስጮህ ከአጠገቤ የሚተኛው ጓደኛዬ ሰምቶኝ ኖሮ አይዞህ፣ እንጅ በማለት ሲቀሰቅሰኝ፣ በገሃዱ ዓለም የሆነ መሰለኝና በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፡፡ በማለት አማተብሁና ተነስቼ ተቀመጥሁ፡፡

አዕምሮዬ መረጋጋት ሲጀምር ምን ሊለኝ ነው? እንደዚህ የሚያቃጀኝ አልሁና‹ መልሼ እፎይ! እንኳንም በህልሜ ሆነ፡፡ በውኔ ቢሆን ኖሮ ምን ሊውጠኝ ነበር፡፡ በማለት እብሰከሰክ ጀመር፡፡ የቀሰቀሰኝ ልጅም እንቅልፉን ስላልጨረሰ ተመልሶ ተኛ፡፡ እኔ ግን እንደገና ለመተኛት ባስብም በህልሜ ያዬሁት ነብር ተመልሶ የሚመጣ ስለመሰለኝ ዐይኔ ፈጥጦ እንቅልፍ የሚባል ነገር እምቢ አለኝ፡፡ ከአንዱ ጎኔ ወደ ሌላው ጎኔ እየተገላበጥሁ የሆነ ያልሆነውን ኃሳብ ሣወጣ ሣወርድ እየደከመኝ መጣና ሊነጋ ጎህ ሲቀድ የእንቅልፍ ሰመመን ይዞኝ ሄደ፡፡ የነቃሁት ጠዋት ሁሉም ለቁርስ ለመሄድ ሽር ጉድ ሲል ነው፡፡ እኔም ተነሣሁና አልጋዬን አንጥፌ ፊቴን ታጠብሁና ለቁርስ ወደ ምግብ ቤት አመራሁ፡፡ ምግብ ቤት እንደ ገባሁ ከምግብ ማደያው አካባቢ ከፍተኛ የሆነ ግርግር በመፈጠሩና ሁሉም ወደዚያ በመሰባሰቡ ምክንያት የምግብ እደላው ለተወሰኑ ደቂቃዎች ተቋርጦ ቆዬና እንደገና ጀመረ፡፡

ግርግሩ ምን እንደሆነ ለማየት ብዙ ተማሪ እየተተራመሰ ስለተሰባሰበ ምን እንደተፈጠረ ለማወቅ አስቸጋሪ ሆነ፡፡ ወዲያው አንዷን ተማሪ ወገቧን፣ እጅና እግሯን ይዘው እያንዘባዘቡ ወደ በሩ ተሸክመዋት መጡ፡፡ በመቀጠልም ወሬ አዳማቂዎች የሚጥል በሽታ ስላለባት ጅው ብላ ስትወድቅ ወደ ባንኮኒው ባይሆን ኖሮ ወለሉ ጭንቅላቷን ቢላት ይሄኔ በሕይወት አትኖርም ነበር፡፡ እያሉ ያወራሉ፡፡ መቼም እንደዚህ ዓይነት ክስተት ሲፈጠር ነገሩን ማዳነቅና ማጋነን የተለመደ ነገር ነው፡፡ በማለት ከፊት ለፊቴ ያለው ተማሪ በእጅጉ ተበሣጨ፡፡ እኔም ቢያወሩ ምን ችግር አለው እንደዚህ የሚናደድ ነገር አይመስለኝም በማለት ታዘብሁት፡፡

የዕለቱ ቁርስ ፍርፍር በዳቦ ሆኖ ሻይውም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሞቅ ያለ ነው፡፡ ቁርስ ፍር ፍር በዳቦ ሲሆን ተማሪው በጣም ይወደዋል፡፡ ለዚህም ይመስለኛል እኔን ጨምሮ ሁሉም በደስታ እየተመገበ ያለው፡፡

ከምግብ ቤት ስወጣ የክላስ ጊዜ እየደረሰ ስለሆነ አብዛኛው ተማሪ እጁን በድንብ ሣይታጠብ ለስሙ ውኃ እያስነካ ይሯሯጣል፡፡ አንዳንዶችም ካለው የጊዜ ጥበት የተነሣ ይባስ ብለው ውኃም ሳያስነኩት በወረቀት ቢጤ ጠራርገውት ይሄዳሉ፡፡ እኔም እንደዚሁ ሌሎችን በመከተል በሩጫ ክፍል ስደርስ መምህሩ ገና አልገቡም፡፡ ከዚያም ክፍል ገብቼ እንደተቀመጥሁ ክፍሉ ምግብ፣ ምግብ ይሸታል፡፡

በዚህም ምክንያት አንደኛው ተማሪ ተነስቶ በማጨብጨብ ሁሉም ተማሪ ፀጥ ሲል ማሳሰቢያ፡ - ከዛሬ በኋላ ማንኛውም ተማሪ ምግብ ከበላ በኋላ እጁን በደንብ መታጠብ አለበት፡፡ ይህ ተግባራዊ ካልሆነ ግን እጁን ያልታጠበው ተማሪ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከሕክምና ተማሪነቱ እንደሚሠረዝ በጥብቅ እናስታውቃለን፡፡ ካለ በኋላ መልዕክቱ የተላለፈው ከዚህ ክፍል እንባ ጠባቂዎች ማህበር ነው፡፡ በማለት ቁጭ ሲል ሁሉም ሣቅ በሣቅ ሆነ፡፡

በዚህ መካከል መምህሩ ገቡና ከወዲያ ወዲህ በመመልከት እንዴት ነው ዛሬ ቁርሣችሁን እዚህ ነው የበላችሁት እንዴ? ሲሉ ቀደም ብሎ የተጀመረውና በእሳቸው መግባት ተቋርጦ የነበረው ሣቅ እንደገና ቀጠለ፡፡ መምህሩም ግራ በመጋባት አብረው ሲስቁ ቆዩና የተናገርሁት ቃል ይህን ያህል ያስቃል እንዴ? ሲሉ አንደኛው ተማሪ፣ ‹‹ቀደም ብለን እኛም እየተነጋገርንበት ስለነበረና እርስዎም ሲደግሙት ነገሩ ገርሞን ነው፡፡ አለና ችግሩ የተከሰተው ሁሌ ፍርፍር በዳቦ ሲሆን ቁርሱን የሚቀጣው ሁሉ ስለሚበላ ሰልፉ ይበዛና ወረፋ ይሆናል፡፡ በዚህም ምክንያት አብዛኛው ተማሪ ተመግቦ እንደወጣ ስለሚረፍድበት እጁን ሣይታጠብ ስለሚመጣ ነው፡፡ ››አለና ‹‹ለወደፊት ግን ከዚህ አድራጎቱ የማይቆጠብ ካለ ከሕክምና ተማሪነቱ ይሠረዛል በሚል ተወስኗል፡፡ ›› ሲል መምህሩም ሲስቁ ቆዩና ነገሩ ጥሩ ነው ግን ቅጣቱ በጣም በዝቷል ባይሆን አንድ ሴሚስተር በሚል ቢሻሻል ሲሉ ሁሉም በስሜት አንዴ አጨበጨበ፡፡ መምህሩም እንደገና አብረው ሲስቁ በመቆየት፤ ተማሪዎች ፀጥ እንዲሉ እጃቸውን ወደ ላይ ሲያሳዩ ሁሉም ዝም አለ፡፡

በሚቀጥለው እትም ይቀጥላል!!!

**የእኔ እይታ፡** በዚህ አምድ ስር የሚቀርቡ ፅሁፎች የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ የራሱን ሀሳብና እይታ የሚያንጸባርቅበት ነው፡፡ የሚወጡት ፅሁፎችም የጋዜጣውን አቋም አያንፀባርቁም!

# እኔ እንዲህ እላለሁ! (አንድ)

## (በትምህርት ላይ ያለ መምህር ትኩረቱ ምን መሆን አለበት - መማር፣ ማስተማር፣ መመራመር፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ በኃላፊነት መስራት ...?)

አበባው ይርጋ አዳሙ (ዶ/ር)
ትምህርትና ስነባህርይ ፋኩልቲ

### መግቢያ

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የማቀርበው ትችትና አስተያየት የሚያነበው በትምህርት ብዙ የተጓዘ ማህብረሰብ እንደሆነ ባምንም ከስንዴ መሃል እንክርዳድ አይጠፋምና "ይሄ እነእከሌን ለማለት ነው፤ ይሄ ደግሞ እኛን ለመንካት ነው" እያሉ ከማንበብ ይልቅ፣ የሚባለው ነገር እውነትነት አለው ወይ? ካለስ ድክመት ነው ወይ? ድክመት ከሆነስ እንዲሻሻል የተጠቆመው ሃሳብ በቂ ነው ወይ? በቂ ካልሆነ ሌላ ምን አማራጭ አለ? የሚለው ላይ እናተኩር ስንል ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡ ጠቃሚውና የጽሁፉም ዓላማ መሰል ጉዳዮችን ባመንሳት መወያየትና በጋራ የተሻለ መፍትሄ መፈለግ ነውና፡፡ በዚህ ጽሁፍ በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ ሊሻሻሉ ይገባል ከምላቸው ጉዳዮች መካከል አንዳንዶቹን አነሳለሁ፡፡ እነዚህ ጉዳዮች ምናልባት በተለያዩ መድረኮች በመምህራን ተነስተው ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በድጋሚ መቅረባቸውን የሚጠላ ያለ አይመስለንም፡፡ ምክንያቱም ሃሳቦቹ ምናልባትም ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህብረሰብ ባለበት ተነስተው ላይሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም ስለጉዳዮቹ በቃል የነገርናቸው ኃላፊዎች ቦታቸውን ለተተኪዎች ለቀው ሄደው ሊሆን ይችላል፡፡ ምናልባትም የሚመለከታቸው ኃላፊዎች ጥያቄዎቻችንና ሃሳቦቻችንን ረስተዋቸው ይሆናል፡፡ ምናልባትም ስህተቶቻችን እንደደንብ ወይም ስርዓት ተወስደው ይሆናል፡፡ ምናልባትም... ምናልባትም... ፡፡ ስለሆነም "በቃል ያለ ይረሳል በጽሁፍ ያለ ይወሳል" እንዲሉ በድጋሚ የሚቀርብ ሃሳብ ካለ በጽሁፍ ነውና አንጥላው፡፡ ነገና ከነገወዲያ ነገሮች ሳይሻሻሉ ከቀሩ የሚመለከታቸውን አካላት የምንሞግትባቸው፣ ተሻሽለው ስናይ ደግሞ የገንቢ ሃሳብ ተቀባይነታቸውን የምናሞካሽባቸው ማስረጃዎቻችን ናቸውና እንዲህ እላለሁ፡፡

የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል ከሚያስፈልጉ አንዱና ዋነኛው ግብዓት ጥራት ያለው መምህር (quality teacher) ነው፡፡ ይህንን ለማሳካት ከሚተገበሩ አበይት ክንዋኔዎች መካከል አንዱ መምህራን ያላቸውን የትምህርት ደረጃ እንዲያሻሽሉ የትምህርትና የተከታታይ ሙያዊ ስልጠና ዕድል መስጠት ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ የተከታታይ ሙያዊ ስልጠና ባህሉ እምብዛም ያልዳበረ ሲሆን፣ መምህራን የማስተርስና የፒኤችዲ (የዶክትሬት) ዲግሪያቸውን በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገር እንዲማሩ ማድረግ ወይም ሁኔታዎችን ማመቻቸት ግን ዋነኛና አስመስጋኝ ስራ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ይበልጥ የሚያስመሰግነው ደግሞ በመርህ ደረጃ መምህራን በትምህርት ላይ ሲሆኑ ከዩኒቨርሲቲው ስራዎች ሙሉ በሙሉ ወይም በከፍተኛ ደረጃ ነጻ እንዲሆኑ ማድረጉ ነው፡፡ የዚህ ጽሁፍ ዋነኛ ትኩረትም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ መምህራን ትኩረት ምን ላይ ነው፣ ያለው ተሞክሮስ ምን ይመስላል በሚሉትና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ የማስተርስና የፒኤችዲ ዲግሪያቸውን ከሚከታተሉ መምህራን መካከልም የዩኒቨርሲቲውንና የጽሁፉን አውድ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ ይህ ጽሁፉ የፒኤችዲ ዲግሪያቸውን በሚከታተሉ መምህራን ላይ ብቻ የተወሰነ እንደሆነ ማስታወስ ተገቢ ነው፡፡

### የፒኤችዲ ዲግሪ ተማሪ ትኩረቱ ምን ላይ መሆን አለበት?

"ጉዳዩ ለቀባሪ አረዱት" ቢሆንም እንዲህ እላለሁ፡፡ የፒኤችዲ ተማሪዎች ለትምህርቱ አስፈላጊ የሆኑ ኮርሶችን በወቅቱ ማጠናቀቅ፣ የደረሱበትን የምርምር ደረጃ በተለያዩ የፒኤችዲ ተማሪዎች ሴሚናሮች ላይ በማቅረብ ከጓደኞቻቸውና ከአማካሪዎቻቸው ምጋቤ ምላሽ ማግኘት ምርምራቸውን

> በመርህ ደረጃ ዩኒቨርሲቲው እነዚህን መምህራን ከተመደበው የስራ ጫና በላይ እንዲሰሩ የማስገደድ መብት የለውም፤ መምህራኑም በዩኒቨርሲቲው ከተወሰነው በላይ የስራ ጫና ይሰጠን ብለው የመጠየቅ መብት የላቸውም፡፡

የበለጠ ውጤታማ ማድረግ፣ የምርምር ውጤቶቻቸውን በተለያዩ ኮንፈረንሶች ላይ በማቅረብ ማስተዋወቅ፣ ምጋቤ ምላሽ ማግኘት እንዲሁም በተለያዩ ተገቢና አካዳሚያዊ በሆኑ ጆርናሎች (አስፈላጊ ሲሆን አካዳሚያዊ ባልሆኑም ቢሆን) ላይ ማሳተምና የመመረቂያ ጽሁፋቸውም ብዙ ፋይዳ ያለው (ለምሳሌ ለምርምር፣ ለማስተማሪያነትና ተግባራዊ እርምጃዎችን ለመውሰድ) ስለሆነ አውቀውና በጥንቃቄ እንዲሰሩ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ለዚህም ነው የፒኤችዲ ትምህርት ብዙ የማንበቢያ ጊዜን የሚፈልግ፣ እውቀትን የሚፈትሽና በሚደረገው የምርምር መስክ ላለው ዕውቀት አስተዋጽኦ ማድረግን የሚጠይቅ ከፍ ያለ የትምህርት እርከን ሆኖ የምናገኘው፡፡ ስለሆነም የፒኤችዲ ዲግሪ ተማሪ ዋነኛ ትኩረቱ በሚማረው ትምህርትና በሚያደርገው የምርምር ስራ ላይ መሆን አለበት፡፡

### የፒኤችዲ ዲግሪ ተማሪ ትኩረት በዩኒቨርሲቲያችን

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የሚነሱ ሃሳቦችን አብራርቶ ለማቅረብና በተሻለ መልኩ ለማስረዳት ሲባል የፒኤችዲ ዲግሪያቸውን በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ የሚከታተሉ መምህራንን በሶስት ከፍለን እንመለከታለን፡፡

#### 1ኛ) ትምህርታቸውን በውጭ ሃገር የሚከታተሉ መምህራን -

እነዚህ መምህራን በትምህርት ዕረፍት (study leave) ምክንያት ለተወሰነ ጊዜ ዩኒቨርሲቲውን ለቀው ስለሚሄዱ ትምህርታቸውን አጠናቀው እስኪመለሱ ድረስ ምንም ዓይነት ተጨማሪ ስራ እንዲሰሩ በዩኒቨርሲቲው አይገደዱም፡፡ እንዲህ መሆኑ የመምህራኑ ሙሉ ትኩረት በሚከታተሉት ትምህርትና በሚያደርጉት የምርምር ስራ ላይ እንዲሆን ያግዛል፡፡ ይህ ደግሞ ትምህርታቸውን ትምህርቱ በሚፈልገውና ዩኒቨርሲቲው በሰጣቸው የትምህርት ውል ጊዜ ውስጥ እንዲያጠናቅቁ እንዲሁም ቀደም ሲል ከነበራቸው የተሻለ እውቀት፣ ክህሎትና ብቃት ይዘው ቶሎ ተመልሰው ተማሪዎቻቸውን እንዲያስተምሩና የተለያዩ ምርምሮችን እንዲያካሂዱ ትልቅ እገዛ ያደርጋል፡፡ መምህራኑ ከዩኒቨርሲቲው ጋር በገቡት የውል ጊዜ ውስጥ ትምህርታቸውን ማጠናቀቅ ካልቻሉ፣ ይህ ለምን ሊሆን እንደቻለ በቂ ምክንያት ከማስረጃ ጋር ለዩኒቨርሲቲው እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አሰራር መልካም ነው፡፡ ከዩኒቨርሲቲው ጋር የትምህርት ውል ይዘው በውጭ ሃገር የፒኤችዲ ትምህርታቸውን ከተከታተሉ መምህራን መካከል አብዛኛዎቹ ትምህርታቸውን በተሰጣቸው የጊዜ ገደብ እንደሚያጠናቅቁ ለተወሰነ ጊዜ ቢያራዝሙ እንኳን ለመራዘሙ አሳማኝ ምክንያት እንደሚያቀርቡ ከስራ ባልደረቦቻችንና ቀደም ሲል በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በኃላፊነት ቦታ ላይ ከሰሩ ግለሰቦች ጋር ካደረግነው ኢመደበኛ ውይይት ለመረዳት ችያለሁ፡፡

#### 2ኛ) ትምህርታቸውን በሀገር ውስጥ ባሉ ዩኒቨርሲቲዎች (ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ውጭ) የሚከታተሉ መምህራን -

በዚህ መልኩ ትምህርታቸውን የሚከታተሉ አብዛኛዎቹ መምህራን በተለያዩ ምክንያቶች ብዙ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በባህር ዳር እንደሆነ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ምንም እንኳን በትምህርት ዕረፍት (study leave) ላይ ቢሆኑም ርቀው ስለማይርቁ የተወሰኑ መምህራን በዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማር ሂደትና በማማከር ስራ በስፋት እንዲሁም በተወሰነ መልኩ በኃላፊነት ስራዎች ላይ ሲሳተፉ ይስተዋላል፡፡ እዚህ ጋር አንድ ተጠየቅ (logic) እናንሳ፡፡ መምህራኑ ለትምህርት ሲላኩ የላካቸው የትምህርት ክፍል የመማር ማስተማሩን ስራዎች በዋነኝነት በስራ ላይ ባሉ መምህራ (fulltime academic staff) ሊያከናውን እንደሚችል ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች የትምህርት ክፍሉን ዕቅድ ተግባራዊነት የሚገዳደሩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ግን የመማር ማስተማሩን ሂደት ለማሳለጥ ሲባል ሌሎች አማራጮችን ሊጠቀም ይችላል፡፡ ከአማራጮች አንዱ በትምህርት ላይ ያሉና በዩኒቨርሲቲው አካባቢ የሚገኙ መምህራን የሚከታተሉትን ትምህርትና የሚያደርጉትን የምርምር ስራ በጣም በማይጎዳ መልኩ የመማር ማስተማሩንና የማማከር ስራውን እንዲያግዙ መጠየቅ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በየትኛውም ስሌት እነዚህ መምህራን የሙሉ ጊዜ ሰራተኛ ከሆኑት መምህራን እኩል ወይም የበለጠ የማስተማርና የማማከር ስራ እንዲሰሩ ማድረግ ምክንያታዊ ካለመሆኑም ባሻገር መምህራኑ የሚማሩትን ትምህርት እንዲሁም የሚያስተምሩትንና የሚያማክሩትን ተማሪ መጉዳቱ "የሮኬት ሳይንስ አይደለምና" ለመረዳት እምብዛም አያዳግትም፡፡

ከእነዚህ መምህራን ጋር ተያይዞ በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ ባሉት ኮሌጆችና ፋኩልቲዎች ያለው ነባራዊ ሁኔታ ምን ይመስላል ብለን ስንጠይቅ መልሱ በዚህ አንቀጽ መጀመሪያ አካባቢ ለመግለጽ እንደተሞከረው አንዳንድ መምህራን የሙሉ ጊዜ መምህር እስኪመስሉን ወይም በትምህርት ላይ መሆናቸውን ፈጽሞ እስክንረሳ ድረስ በዩኒቨርሲቲው የመማር ማስተማር ሂደት፣ የማማከርና የምርምር ፕሮጀክቶች ውስጥ በስፋት እንዲሁም በተወሰነ መልኩ በኃላፊነት ቦታዎች ላይ ሲሳተፉ እናስተውላለን፡፡ ይህ ደግሞ የሚማሩትን ትምህርትና የሚያደርጉትን ምርምር ትዝብት ላይ የሚጥል ከመሆኑም በላይ በሁሉም መስክ የተሳካ ውጤት እንዳይመዘገብ ስለሚያደርግ ሊታረም ይገባዋል፡፡

#### 3ኛ) ትምህርታቸውን በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲና በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ሳውዝ አፍሪካ (UNISA) የሚከታተሉ መምህራን -

እነዚህ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲና በዩኒቨርሲቲ ኦፍ ሳውዝ አፍሪካ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# BDU colorfully celebrated Ethiopian Nations, Nationalities and Peoples Day



















BDU's College of Health & Medical Sciences and FelegeHiwot Hospital signing an advanced Memorandum of Understanding (MoU)



Community of the university participating in football match for HIV/AIDS awareness creation campaign



The President of the ANRS, HE Mr. Gedu Andargachew, addressing participants at the workshop focusing on the multidimensional urban poverty analysis in the region

# እኔ እንዲህ እላለሁ! ...

ከገጽ 7 የዞረ

ትምህርታቸውንየሚከታተሉ መምህራን ትምህርታቸውንና የምርምር ስራቸውን የሚያደርጉት ከላይ በተራ ቁጥር አንድና ሁለት እንደተጠቀሱት ዩኒቨርሲቲውን በትምህርት ዕረፍት (study leave) ምክንያት ለቀው በመሄድ አይደለም፡፡ እነዚህ መምህራን የሚከታተሉት ትምህርትና የሚያደርጉት የምርምር ስራ የሚፈልገውን ከፍተኛ ጊዜ ከግምት ውስጥ በማስገባት ዩኒቨርሲቲው አብዛኛውን ጊዜያቸውን በዚሁ ላይ እንዲያሳልፉ ያደርጋል፡፡ በዚህ መሰረት መምህራን እንዲሰሩ ከሚጠበቅባቸው መደበኛ ጫና ውስጥ ሶስት ክሬዲት ሃወር ብቻ እንዲይዙ ይደረጋል፡፡ በመሆኑም በመርህ ደረጃ ዩኒቨርሲቲው እነዚህን መምህራን ከተመደበው የስራ ጫና በላይ እንዲሰሩ የማስገደድ መብት የለውም፤ መምህራኑም በዩኒቨርሲቲው ከተወሰነው በላይ የስራ ጫና ይሰጠን ብለው የመጠየቅ መብት የላቸውም፡፡ በዚህ ሁላችንም እንስማማለን ምክንያቱም የዩኒቨርሲቲው መተዳደሪያ ደንብ ለዚህ እንድንገዛ ስለሚያደርገን፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደጠቀስነው በተለያዩ ምክንያቶች ትምህርት ክፍላቸው የእነዚህ መምህራን ተጨማሪ እገዛ እጅግ በጣም ካስፈለገው አቅርቦ ሊያወያያቸውና ትምህርታቸውንና የምርምር ስራቸውን ብዙም በማይጎዳ መልኩ በጣም ውስን ተጨማሪ ክሬዲት ሃወር እንዲይዙ ሊጠይቅ ወይም ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ይህ የሚሆነው ግን በሙሉ ጊዜ የሚሰሩ መምህራን ያላቸው የስራ ጫና እጅግ የተጋነነ ሲሆን ወይም ኮርሱን በሙሉ ጊዜ ከሚያስተምሩ መምህራን መካከል ሊሰጥ የሚችል ብቁ መምህር የለም ተብሎ ሲታሰብ ወይም ሌላ እጅግ አስቸጋሪ የሚባል ሁኔታ ሲገጥም ብቻ ነው፡፡ እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታ ካልገጠመና በሙሉ ጊዜ የሚያገለግሉ መምህራን ያለውን የማስተማርና የማማከር ስራ አይወጡትም የሚል አሳማኝ ሁኔታና ማስረጃ ካልቀረበ በቀር ከላይ በተጠቀሱት በየትኛውም ምድብ ውስጥ የሚገኙ መምህራን ጊዜያቸውን በሚማሩት ትምህርትና በሚያደርጉት ምርምር ላይ እንዲያደርጉ ማድረግ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ነው፡፡ ያኔ ነው ይበልጥ ውጤታማ የሚሆኑትና በቀጣይነት ዩኒቨርሲቲውንም በበለጠ እውቀት፣ ክህሎትና ብቃት የሚያገለግሉት፡፡

በየትኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም እንደሚደረገው በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ መምህራን ከማስተማርና ከመመራመር በተጨማሪ በተለያዩ ዕርከኖች ላይ በሚገኙ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ተመድበው ይሰራሉ፡፡ በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ በሙሉ ጊዜ ከሚያገለግሉ መምህራን መካከል የተፈለገውን የኃላፊነት ቦታ ሊሸፍንና ሊሰራ የሚችል ሰው የለም ብሎ ዩኒቨርሲቲው ካመነ ብቻ ነው በትምህርት ላይ ያሉ መምህራንን ለኃላፊነት ቦታው ሊጋብዛቸው የሚገባው፡፡ እንዲህ ዓይነት አጋጣሚዎች ደግሞ የማይታሰቡና ቢኖሩም ዕድላቸው ከሺህ አንድ ያነሰ ነው የሚል እምነት አለኝ፡፡ ይህ እንኳን ቢሆን ዩኒቨርሲቲው የሚጥልባቸውን ኃላፊነትና የማስተማርና የማማከር ስራቸውን በብቃት እንዲወጡ ለማስቻል ሲባል ትምህርታቸውን ለተወሰነ ጊዜ እንዲያቋርጡ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡ እዚህ ላይም በመርህ ደረጃ በትምህርት ላይ ያለ መምህር በኃላፊነት ቦታ ላይ ልስራ ብሎ የመጠየቅ መብት አለው ብዬ አላስብም፡፡ ምክንያቱም የፒኤችዲ ዲግሪ ትምህርትና ምርምርም ሆነ ኃላፊነት በየራሳቸው ትልቅ ጫና የሚፈጥሩና አብረው የሚሄዱ ባለመሆናቸው ነው፡፡ በዩኒቨርሲቲያችን ውስጥ ያለው ተሞክሮ ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው፡፡ በሃገር ውስጥ የሚማሩ መምህራን ተጨማሪ የማስተማርና የማማከር ስራን እንዲሁም በኃላፊነት መስራት ይፈልጋሉ፡፡ አልፎ ተርፎም ከሙሉ ጊዜ መምህራን እኩል ወይም በላይ ጫና ካልያዝን ብለው ሽንጣቸውን ገትረው ሲሟገቱና በዚህም ውጤታማ ሲሆኑ ማየት አንገት የሚያስደፋና ምን እየተደረገ ነው ያለው ብለን እንድንጠይቅ የሚያደርግ ነው፡፡ ለዚህ አስረጅ የሚሆነን በየኮሌጅና ፋኩልቲያችን አሁን በሙሉ ጊዜ ስራና በትምህርት ላይ ያሉ መምህራን የያዙትን የማስተማርና የማማከር የስራ ብዛት ማነጻጸርና ምን ያህሉ በትምህርት ላይ ያሉ መምህራን በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ አሉ የሚለውን ማየቱ ነው፡፡

በተራ ቁጥር ሁለት እንደተጠቀሰው ሁሉ ተማሪ መሆናቸው የሚያውቁት እነሱና የሚያስተምሯቸው መምህራን ብቻ እስኪሆን ድረስ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ባሉ የመማር ማስተማርና የኃላፊነት ስራዎች ላይ ተጠምደው ወጤታማ እንዳይሆኑ ስለሚያደርጋቸው አንድ ሊባል ይገባል፡፡ አንድ የፒኤችዲ ተማሪ ከፍተኛ ጫና ይዞ ሲያስተምር፣ የመጀመሪያና የማስተርስ ዲግሪ ተማሪዎችን ሲያማክር፣ ከኮርስ አስተባባሪነት እስከ ከፍተኛ ኃላፊነት ቦታ ላይ ተቀምጦ ሲሰራና ከዩኒቨርሲቲው ለምርምር የሚውል ገንዘብ ወስዶ ሌላ ተጨማሪ ምርምሮች ላይ ሲሳተፍ ማየት ብርቅ ባልሆነበት ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የፒኤችዲ ተማሪነት ምንድን ነው? ትኩረቱስ ምን ላይ ነው ብለን እንጠይቃለን፡፡ ተሞክሮዎች እንደሚሳዩት በዚህ ምድብ ውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ መምህራን የትርፍ ጊዜ ስራቸው የሚያስተምሩት፣ የሚያማክሩት ወይም የያዙት የኃላፊነት ቦታ ሳይሆን እየተራከሰ ያለው የፒኤችዲ ትምህርት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

## እንደማጠቃለያ

መምህራን የተሻለ እውቀት፣ ክህሎትና ብቃት ኖሯቸው ጥራት ያለው ትምህርት መስጠት እንዲችሉ ለማድረግ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ ከነዚህም መካከል አንዱና ዋነኛው መምህራን ያላቸውን የትምህርት ደረጃ እንዲያሻሽሉ ዕድል መስጠት ነው፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ በተቻለ መጠን ሙሉ ጊዜና ትኩረታቸውን በትምህርትና ምርምራቸው ላይ እንዲያደርጉ አስፈላጊውን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ ነው፡፡ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ያለበቂ ምክንያት በትምህርት ላይ ያሉ መምህራን ከጫና በላይ እንዲያስተምሩ፣ እንዲያማክሩ ይባስ ብሎም በኃላፊነት እንዲሰሩ ማድረግ ግን ለሚማሩት ትምህርት ሲባል የስራ ጫና እንዲቀነስላቸው የተደረገበትን ተጠየቅ (logic) ከመሰረቱ የሚያፋልስና በመርህ አለመመራትን የሚያመለክት ነው፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ልናሳካው የምንጥረውን የትምህርት ጥራት የሚገዳደር ነው፡፡ እኛ እንደምናስበውና እንደሚገባን በትምህርት ላይ ያሉ መምህራንን በኃላፊነት ቦታ ላይ ማስቀመጥ የሚከታተሉትን የትምህርት እርከን ማራከስና የሚያደርጉትን ምርምርና የሚሰጣቸውን የኃላፊነት ቦታም መናቅ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ ምንስ ሊሆን ይችላል? እንዲህ ዓይነቱ አካሄድ በየትኛውም መልኩ ለዩኒቨርሲቲው አዋጭ አይደለም፡፡ በጥናት የተደገፈም ባይሆን ፒኤችዲ መማርን፣ ምርምር ማድረግን፣ ከጫና በላይ ማስተማርና ማማከርንና ኃላፊነትን አብረው ሊያስኬዱ የሞከሩ መምህራን ትምህርታቸውን ሲያቋርጡ ወይም ከሚገባው ጊዜ በላይ ያለ በቂ ምክንያት ሲያራዝሙ ማስተዋሉ የጓዳችን ታሪክ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቢያንስ የህሊና ተጠያቂ የሚያደርግ የሃገራዊ ሃብት ብክነት ነው፡፡

በዚህ ጽሁፍ ለመዳሰስ እንደተሞከረው በትምህርት ላይ ያሉ መምህራን ከጫና በላይ በመማር ማስተማርና በኃላፊነት ቦታዎች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ በርካታ ተግዳሮቶች ያሉትና ብዙ መርሆችንና ተጠየቆችን የሚጥስ ቢሆንም፣ እንቆቅልሹ በትምህርት ላይ ያሉ መምህራን ከጫና በላይና በኃላፊነት መስራት እንደ መብት መታየቱ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በመምህራኑ ብቻ ሳይሆን በዩኒቨርሲቲው በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች ላይ ባሉ ግለሰቦች ጭምር የሚንጸባረቅ ግንዛቤ ነው፡፡ ለእንዲህ አይነቱ አዳካሚ አካሄድ ዋቢ የሚደረገው ደግሞ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ይህ እንዳይሆን የሚከለክል መተዳደሪያ ደንብ ወይም መመሪያ የለም የሚል ሃሳብ ነው፡፡ እዚህ ላይ በዋናነት ልንረዳው የሚገባን እየሄድንበት ያለነው መንገድ ትክክል ነው ወይ የሚለውን ነው፡፡ አካሄዱ ስህተት መሆኑን መረዳት ከቻልን የደንብና መመሪያ አለመኖርን ስህተትን በስህተትን ማረሚያ ዘዴ አድርጎ መውሰድ ተገቢ አይደለም፡፡ እንዲህ አይነት አካሄድ የምናስበውና የምናልመው እየሆንን ካለነው ጋር የሚጣረስብን ያደርገናል፡፡ አስፈላጊነቱ ከታመነበት የኛው ፍጡር የሆነው ደንብና መመሪያ የማይስተካከልበት ምንም ምክንያት አይታየኝም፡፡

ዩኒቨርሲቲው የፒኤችዲ ተማሪዎች ሙሉ ትኩረታቸውንበትምህርታቸው ላይ እንዲያደርጉ ለማድረግ ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች ተሞክሮ በመውሰድ (ለምሳሌ የሐሮማያ ዩኒቨርሲቲን) ችግሩን መቅረፍ ይኖርበታል፡፡ የሚመለከታቸውም የችግሩን አሳሳቢነት ተረድተው መፍትሔ ይሰጡታል ተብሎ ይታሰባል፡፡ ምክንያቱም መልካም ነገር ማሰብና መፈጸም የሁላችንም የዜግነትና ተቋማዊ ግዴታችን ነውና!

ቸር እንሰንብት!

# የ ግ ጥ ም ጥ ግ

## መምህሩን እንምሰል

መምህሩ ከጨለማው ወደ ብርሃኑ

ወገኑን አክባሪ እያለ 'ወደኔኑ

ከችግር ከድንቁርናው እንድትድኑ፡፡'

መምህሩ የቀለም አባት በከተማው በገጠሩ፣

በማካፈልና በማባዛት በመቀነስ በመደመሩ፣

ጨለማን አባራሪ የብርሃን ሰው መምህሩ

እውቀት አምራች በወገኑ በሀገሩ

መምህሩ በሁሉም ቦታ አለኝታ ነው

አናጢም ግንበኛም ነው

ወታደርም ስቢልም ነው

በምድር በባህር በአየርም በራሪ እና አብራሪም ነው

ለህሙማን ሐኪም ፈዋሽም ነው፡፡

መምህሩ በጦር ሜዳውም እኮ አለ

በካርታ እና በኮንፓስ የሀገሩ ዳር ድንበሩን እያስከለለ፣

ወሰናችን ከእስከ ነው እያለ

በእርሻ ቦታው በፋብሪካውም እናምርት እያለ

ከዳኞች ጋር ዳኛ ሁኖ አብሮ አለ

ድሀ እንዳይበደል ፍርድ እንዳይጓደል እያለ

መምህሩ የሌለበት ቦታ የለም በሁሉም ቦታ አለ

ተማሩ እንማር እያለ፡፡

## እድሜ ያስተምራል

እድሜ አስተማሪ ነው በእድሜው ከሰራበት

ታሪክን ለትውልድ ካስተላለፈበት

ሰምቶ ለሚያሰማ አይቶ ላሳየበት

በአሉባልታ ወሬ በሀሜት በትችት፣ ካልተቃጠለበት

ፆታና ሀይማኖት ዘር ካልቆጠረበት

የተጣላ አስታርቆ ምክር ትምህርት ከሰጠበት

እድሜ አስተማሪ ነው ከመጥፎው ርቆ ጥሩ ከሰራበት፡፡

በእድሜአቸው ያልሰሩ እድሜ ሰርቶባቸው

በታሪክ በትውልድ ተወቃሾች ናቸው፡፡

ሰርታችሁ እለፉ ስራ ያልሰራችሁ

በጊዜአችሁ ስሩ ጊዜ አይስራባችሁ

እኔም የድርሻየን ይችን ላኩላችሁ

አንብቡና ፃፉ ወጣቶች ባካችሁ

በልጅ የልጅ ልጆች ትወቀሳላችሁ

ፀጉር ማፍተልተሉ ገላ መራቆቱ ተውት ይቅርባችሁ፣

ባህልም አዘነ ወላጅም ጠላችሁ፡፡

ከ፲ አለቃ ሞላ መስፍን በኢ.ን.ባ.ክ

*የጉዞ ማስታወሻ*

# ለጎ ሀይቅ - በአንድ ፊት፣ ሁለት መልክ

**ጀማል ሙሀመድ ሀይሌ (ዶ/ር)**
ከጋዜጠኝነትና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል
jemalmohammed99@gmail.com

“ለጎ ሀይቅ ወርጄ፣ ወዲያ ልመንኩሰው
“ባንቻሮ-ባንቻሮ፣ እንዴት ይሞታል ሰው፡፡”

“መኪናችን” አፍንጫዋን ወደ ደቡብ አቅጣጫ አዙራ እየከነፈች ነው፤ እንደ ዘንዶ የተጠማዘዘውን የወልደያ-ደሴን መንገድ ቶሎ-ቶሎ እየሰበሰበችው ነው፡፡ ወሩ ግንቦት (2006) ቢሆንም የመንገዱ ግራና ቀኝ በአብዛኛው ለምለም ነው፡፡ ወቅቱ ከረፋድነት ትንሽ እልፍ እንዳለ - 5 ሰአት አካባቢ - ሀይቅ ከተማ ገባን፤ ከደሴ ከተማ በስተሰሜን አቅጣጫ 30 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ከምትገኘው ሚጢጢዬ ከተማ፡፡ የሀይቅ ከተማ በማይመለስ መንገድ መጠሪያዋን የተዋሰችው በትንሽ ርቀት ላይ ከሚገኘውና “ለጎ ሀይቅ” ተብሎ ከሚጠራው ሀይቅ ነው፡፡

ከላይ ስለሰፈረው ግጥምና ሀይቁ ስላለው ማራኪ ገፅታ አብረውኝ ለሚጓዙት ለሁለቱ የስራ ባልደረቦቼ ሳጫውታቸው ሀይቁን ለመጎብኘት ጉጉት ስላደረባቸው መኪናችን ፊቷን ወደ ምስራቅ በማዞር ወደ ግራ ታጠፈች፡፡ ከአምስት ደቂቃ የበለጠ ሳንጓዝ የሰማይ ስባሪ መስሎ የተንጣለለው ለጎ ሀይቅ ከፊታችን ተዘረጋ፡፡ አቤት ፀጥታው! ወደ ተመልካቹ ልብ ሰላምን በሚያሰርግ ፀጥታ ተሞልቷል፡፡

“ከመኪናችን” ወርደን ወደ ሀይቁ ተጠጋን፡፡ ጥቂት የቀንድ ከብቶችና ፍየሎች ከሀይቁ ዳርቻ ላይ ተሰማርተዋል፡፡ የሀይቁ ዳርቻ በሚታጨድና ከብቶች በሚግጡት ሳር የተሞላ በመሆኑ ጎብኚውን ከሀይቁ የሚለይ አለትም ሆነ ቋጥኝ የለም፡፡ ስለዚህም ከሀይቁ ዳር የቆመ ሰው እንግድነት አይሰማውም፤ ከመጥራቱ የተነሳ ኩል መስሎ የሚታየው የለጎ ሀይቅ ውሀ እዚያው እፊቱ ነው - ጎንበስ ብሎ ሊነካው፣ ሊያንቦጫርቀው በሚያስችለው ርቀት፡፡

ግራና ቀኝ ከሚገኙት ሁለት የመዝናኛ ቦታዎች ወደ አንዱ አመራን፡፡ የዕረፍት ቀን ባለመሆኑ ብዙም ሰው የለም፡፡ የአካባቢው ፀጥታና የባህሩ አማላይነት ከመዝናኛ ቦታው ውበት ጋር ተዳምሮ ቆዳን አልፎ ወደ ደም ስር የሚፈስ ሀሴት ይረጫል፤ “ሁሌም እዚሁ በኖርኩ” ያስብላል፡፡ በጉዞአችን ላይ የሚያማምሩ የገጠር አካባቢዎችን ባለፍን ቁጥር ምኞቱን የሚያስተጋባውን ባልደረባችንን “መኖር እዚህ ነበር” ለማለት የቀደመው የለም፡፡

ወዲያው አሳ አዘዝን - አሳዎች ከውስጡ የሚቦርቁበትና የሚንቧቹበት ለጎ ሀይቅ ዳር ተቀምጦ ማን ሌላ አይነት ምግብ ይበላል? የምናዘውን የምግብ መጠን በተመለከተ፣ ስለአቅርቦቱ ጥራት ከማያውቁት ምግብ ቤት ሲገባ በሚታዘዝበት “ቋንቋ” ለማዘዝ ከባልደረቦቼ ጋር ተስማማን “እስቲ መጀመሪያ አንድ ይምጣ!” በማለት፡፡

አስተናጋጁ ጋሻው ጋር በሁለት ነገር ተስማማን - አንድ ትኩስ አሳ አስጠብሶ ሊያመጣ፤ ሁለት የሚጠበሰው አሳ ደግሞ በጣም ትልቅ ሊሆን፡፡ “ትልቁን አስጠብሳለሁ” በማለት ቃል ሲገባ፣ ከፊታችን ካለው ጠረጴዛ ላይ ክንድ ሊሞላ ትንሽ የሚቀረው ርዝመት በእጆቼ እያሳየሁት “ይሄን የሚያክል?” አልኩት፡፡ አፉን ሞልቶ “አዎ!” አለ፡፡ ፈጠን ብዬ እስኪርቢቶ ከደረት ኪሴ አውጥቼ ከጠረጴዛው ላይ ምልክት ፃፍኩ፡፡ ይህን ያደረኩት ያን ያክል የረዘመ አሳ ይኖረዋል ብዬ ሳይሆን ካሉት አሳዎች ውስጥ የመጨረሻ ትልቁን እንዲያስጠብስልን ግፊት ለመፍጠር ብዬ ነው፡፡ ጋሻው ግን በመገረም ከት ብሎ ሳቀ፡፡

አሳው ተጠብሶ እስከሚዘጋጅ ድረስ በሀይቁ ላይ በጀልባ ትንሽ ብንሸራሸር ጥሩ መሆኑን መከረን - አስተናጋጁ፣ ጋሻው፡፡ ከሀይቁ ላይ የተተከለ ትንሽ ነገር መስሎ የሚታየውን ምልክት አሻግሮ በርቀት እያሳየን “እዚያ ደርሶ ለመመለስ ለአንድ ሰው አስር ብር ብቻ!”…

ከመሬት ወደ ሀይቁ የተወሰኑ ሜትሮች ገባ ብሎ በድንጋይ ካብ የተሰራውን የመንገድ ጠርዝ ጠጋ ብላ ወደ ቆመችው የሞተር ጀልባ አመራን፡፡ ከጀልባዋ ላይ ምን ሊያስተናግደን እንደ ሆነ ባናቅም ጋሻው አብሮን መጣ፡፡ ወደ ጀልባዋ እየተጠጋን እንዳለ ከፊታችን ቀደም ብሎ በመሄድ ልብሱን አወላለቀ - በፓንት ብቻ ሆነ፡፡ ልብሶቹን ከድንጋይ ላይ አስቀመጠ፡፡ እኛ ከጀልባዋ ላይ ስንሳፈር፣ እሱም በሀይቁ ውሀ ውስጥ በመራመድ ወደ ጀልባዋ ተጠጋ፡፡ የጀልባዋን ነጂ አንድ የሆነ ነገር እንዲሰጠው ጠየቀ፤ የሆነ ብረት ነገር ሰጠው፡፡ ብረቱ ቢያንስ በአንድ ጫፉ በኩል የ“ፐ” ቅርፅ ያለው እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡

ጀልባዋ ገና ጉዞዋን ከመጀመሯ ‘ሾፌሩ’ “ጋሻው” ብሎ ከተጣራ በኋላ ስድብ የተቀላቀለባቸው ቃላት ወረወረ፡፡ ዞር ዞር ብለን አየን፤ ጋሻው በደረቱ ከሀይቁ ውሀ ላይ ተደፍቶ፣ እየዋኘ ሳይሆን እየተጎተተ እናም ከጀልባዋ እኩል በሆነ ፍጥነት እየተከተለን ነው፡፡ የ“ፐ” ቅርፅ የሰራውን ብረት (ለብረቱ የ“ፐ” ቅርፅ የሰጡትን ሁለት ጫፎች) በእጆቹ ጨምድዶ ይዟል፡፡ የብረቱ ሌላው ጫፍ ከጀልባዋ የኋላ አካል ጋር ወይ ታስሯል ወይ ደግሞ በሆነ መንገድ ተጠልፏል፡፡ ብቻ የጋሻው እጆች ሊበጠስ እስኪደርስ እንደ ተወጠረ ፕላስቲክ ተለጥጠዋል፡፡ ጀልባዋ እየቀደደች የምታልፍበት ውሀ አፍንጫ-አፍንጫውን፣ ግንባር-ግንባሩን፣ ፊት ፊቱን እየመታው፤ ጀልባዋም ባለ በሌለ ሀይሏ እየጎተተችው ነው፡፡

የመመለሻችን ምልክት እስከምንደርስ ያን እንቅልፍ የወሰደው ያህል ፀጥ ብሎ የተኛ ውሀ እየቀደደች፣ ኩል መስሎ የተንጣለለውን ውሀ አረፋ እያስደፈቀች ጀልባዋ ጉዞዋን ቀጠለች፤ ከጀርባዋ ደግሞ ባለ በሌለ ጉልበቷ ጋሻውን እየጎተተች፣ በሆዷ በምታምቧችረው የሀይቁ ውሀ ፊት-ፊቱን፣ አናት-አናቱን፣ ትከሻ-ትከሻውን እየደበደበችው፡፡

“ሾፌሩ” ከመድረሻ ምልክቱ ትንሽ እልፍ በማለት ከመረቀልን በኋላ ጀልባዋን አቆማት፤ ጀልባዋ አረፈች፤ ጋሻውም ትንሽ ዕረፍት ወሰደ፡፡ እኛም ለቅፅበት ያህል የሀይቁን ውሀ እና አካባቢውን በአይናችን ቃኘን፡፡ የውሀው ጥራት፣ የሀይቁ ዙሪያ ልምላሜ፣ የአካባቢው እርጋታና ፀጥታ… ሁሉም ነገር በብዙ እጥፍ ጨመረብን፡፡ ከለጎ ሀይቅ የሚገኘው ውበትና ፍሰሀ ከፍተኛውን የሙሉእነት ደረጃ የሚያገኘው እዚያ ከሀይቁ እምብርት ላይ ሳይሆን አይቀርም…

በዚህች ሀይቁ ላይ ባለንባት ትንሽ የዕረፍት ቆይታችን ጋሻው ለምን በጀልባ እንደሚጎተት ጠየቅነው፡፡ በዋናተኛነት ይወዳደራል፡፡ እናም በጀልባ መጎተቱ ይህን የዋና ክህሎቱን ይበልጥ ለማዳበር ያግዘዋል፤ የዋናተኛነቱን ሙያ ይበልጥ ለማደበር “ህልም” አለውና፡፡ እንዲህ ያለ ወጣት እንዴት ያስቀናል - ስራ ሳይንቅ አስተናጋጅ ሆኖ ይሰራል፤ አካባቢው የፈጠረለትን መልካም አጋጣሚ በመጠቀምም ህልሙን ሰንቆ አካሉን በስፖርት ያንፃል…

ጀልባዋ በሰሜን አቅጣጫ በኩል በማድረግ የመልስ ጉዞዋን ተያያዘችው፡፡ ጋሻውም እጁ እስኪነቀል እየተጎተተ፣ ጀልባዋ በፍጥነቷ ሳቢያ በምትፈጥረው ማእበል እየተመታ፣ የመልስ ጎዞውን ተያያዘው፡፡

ከጀልባዋ እየወረድን እንዳለ ጋሻው በፍጥነት ለባብሶ ፈትለክ አለ - ወደ ስራው፡፡ ወንበራችንን እንደ ያዝን ያዘዝነውን አሳ ጥብስ ይዞ ከፊታችን ከች፡፡ የተጠበሰው አሳ በጣም ትልቅ ነው፡፡ አነሳሁና ጠረጴዛ ላይ ወደ አስቀመጥኩት ምልከት በማስጠጋት ለካሁ፡፡ ቁመቱ ልክ ነበር፡፡ ቁመቱ ትንሽም ሳይቀንስ ትንሽም ሳይጨምር “መቶ በመቶ” ሊባል በሚችል መጠን እኩል መምጣቱ ሁላችንንም አስገረመን፡፡ ጋሻው ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ሳቅን፡፡

አሳውን አብሮት ከመጣው ዳቦና መጠነኛ አትክልት ጋር እየጠቀለልን፣ በአዋዜው እየተኩምን አወራረድነው፤ አቤት ጥፍጥናው፤ አቤት ማጥገቡ!

የአሳው ምግብ ጥፍጥና፣ የሀይቁ ውሀ ኩል መስሎ መጥራት፣ የሀይቁ አስደማሚ እርጋታ፣ የአካባቢው ማራኪ ፀጥታ ለጎ ሀይቅን የመረጋጋት፣ የሰላምና የፍስሀ ምንጭ አድርጓታል፡፡ አንድ በሚስቱና በኑሮ ምርር ያለ ወሎዬ ከብዙ አመታት በፊት፣

“ለጎ ሀይቅ ወርጄ፣ ወዲያ ልመንኩሰው

“ባንቻሮ-ባንቻሮ፣ እንዴት ይሞታል ሰው”

ብሎ መግጠሙ ለዚህ ይሆን?…

መኪናችን እንደ ልማዷ አፍንጫዋን መጀመሪያ ወደ ሀይቅ ከተማ ከዚያም ወደ ደሴ ቀስራ መክነፍ ስትጀምር፣ ለጎ ሀይቅ ከጀርባች እየራቀ-እየራቀ ሄደ፡፡ ሆኖም ከልባችን ያሰረገው እርካታ፣ ከህሊናችን ያተመው ፍስሀ ግን ከፊታችን ይታየን ነበር - ከመኪናው የፊት መስታዎት ላይ የተለጠፈ ያህል፡፡ ለዚህም ነው የለጎ ሀይቅ “ትረካች” ሳያልቅ ደሴ መግባታችን…

ይህ በሆነ በሁለት ወር ውስጥ ቤተሰብ ለመጠየቅ ልጆቼን ይዤ ወደ ደሴ ጎራ አልኩ፡፡ ደሴ-ኮምቦልቻ እያልን ቤተ ዘመዱን ካየን በኋላ በቀረችን ጊዜ ውስጥ ለጎ ሀይቅን መጎብኘት ይፈልጉ እንደሆን እንደ አንድ አማራጭ አቀረብኩላቸው፡፡ ቦታውን አይተውት ስለማያውቁ ሁሉም በአንድ ድምፅ አፀደቁት፡፡ እናም ጉዞ ከደሴ ወደ ሀይቅ ከተማ ሆነ፣ በእለተ እሁድ እስከ ሀይቅ ከተማ “በሚኒባስ”፣ እስከ ለጎ ሀይቅ “በባጃጅ”፡፡

ከ”ባጃጅ” ውርድ እንዳልን - ገና ተዳፋቱን መውረድ ሳንጀምር - የሚያንቧርቁ የሙዚቃ ድምፆች ተቀበሉን፤ ከሀይቁ ግራና ቀኝ የሚገኙት ሁለት የመዝናኛ ቦታዎች በፉክክር የሚለቁት ሀይለኛ የሙዚቃ ድምፅ፣ አካባቢውን እያናወጠው ነው፡፡ በ“Montarbo” የድምፅ ማጉያዎች እየተስተጋቡ ከሀይቁ ዳር ወደ ላይ የሚለቀቁት የሙዚቃ ድምፆች፤ ሰዎች ሊዝናኑ ሳይሆን የጆሮን ታንቡር በሚበሳ ድምፅ ሊቀጡባቸው የተዘጋጁ ቦታዎች አስመስሏቸዋል፡፡ ለካስ ባዘቦቱ ቀን ጭምት የመሰሉት መዝናኛ ቦታዎች እሁድ-እሁድ ያብዱ ኖሯል፡፡

በግምት ከአስር ሜትር የማይበልጠውን ተዳፋት ደርደር-ደርደር ብለን ወረድንና በስተግራችን በኩል ካለው መዝናኛ ቅጥር ገባን፡፡ ወደ መዝናኛው በዘለቅን፣ ግራ-ቀኙን ባየን ቁጥር፣ አይቶት ለማያውቅ ሰው ያለበትን ቦታ እስኪጠራጠር፣ “በህልሜ ወይስ በውኔ” እስከሚል ድረስ ግራ የሚያገባ ትእይንት ማየት ጀመርን፡፡

ከመዝናኛው ቅጥር ግቢው ውስጥ የተዘጋጁት ጥቂት ወንበሮች ቢራ በመጠጣት ተግባር በተጠመዱ ሰዎች ተይዘዋል፡፡ የተረፈው ቦታ “ሙሉ በሙሉ” ሊባል በሚያስችል ሁኔታ አንጥፈው በተቀመጡ ሰዎች ተሞልቷል፡፡ ከመተላለፊያ ቀጭን መስመር /”መንገድ”/ በስተቀር ባዶ ቦታ የለም፡፡ አብዛኛዎቹ ወጣቶች ሲሆኑ ጥንድ-ጥንድ (ወንድ-ሴት) ሆነው ወይም በጋራ እጅብ-እጅብ ብለው ተቀምጠዋል፡፡ ጥያቄው እንዲህ ምድሩ እስኪጠብ ለምን ተነጠፈ፤ ለምንስ ያ ሁሉ ወንድና ሴት ወጣት ምንጣፍ ላይ ተቀመጠ የሚለው ነው፡፡ መልሱ አጭር ነው - ጫት ሊቅሙ፡፡ “ከነገ ጀምሮ ጫት መቃም ተከልክሏል” ወይም “ከነገ ጀምሮ ጫት ወደማይቃምበት ሌላ አገር ትሄዳላችሁ” የተባሉ

ወደ ገጽ 12 ዞሯል

# ለጎ ሀይቅ - በአንድ ፊት ...

ከገጽ 11 የዞረ

ይመስል ቂምሀውን አጧጡፈውታል፡፡ አንዳንዶቹ የህፃን ልጅ ኳስ የጎረሱ እስኪመስል ድረስ ጉንጫቸውን በጫት አሳብጠውታል፡፡ ሌላው አስገራሚ ነገር የጫት አቅርቦቱ ችግርም የተፈታ መሆኑ ነው፤ እዚያ ከመዝናኛው ደጅ ላይ የተዳጊ ወጣት ቁመት ሊያክል ትንሽ የሚቀረው የረጃጅም ጫት ዛላ ክምር ይዞ የተቀመጠ ወጣት አለ፡፡

ባጭሩ ወጣቱ ጫት ያቀርባል፤ ወጣቱ ይቅማል፤ ወጣቷ ትቀማለች፤ ወጣቷ ታስተናግዳለች፤ ወጣቱ ይስተናገዳል፤ ወጣቱ ይዘፍናል፤ ወጣቶች ይመረቅናሉ፤ ወጣቶች ይሰክራሉ፤ ወጣቶች ይሳከራሉ - በሙዚቃ ላይ ሙዚቃ፣ በጫት ላይ ጫት፣ በቢራ ላይ ቢራ፣ በሲጋራ ላይ ሲጋራ…

ነገሩ በጣም በጣም አስገረመኝ፡፡ ደሴ ተወልጄ እስከ አደግኩ ድረስ ጫት በህብረተሰቡ ውስጥ ስላለው ቦታ አሳምሬ አውቃለሁ፡፡ ቁጥራቸው ይነስም ይብዛ ጫት በመሸጥ የሚተዳደሩ፣ በጫት ንግድ የከሰሩ፣ ጫት ሳይቅሙ መዋል የማይችሉ፣ በጫት ቂምሀ የቤተሰባቸውን ኑሮ ጭምር ያናጉ… ሰዎችን አውቃለሁ፡፡ የአይጥ መርዝ በጥብጦ በመጠጣት ህይወቱን ላጠፋ የቀድሞ ሰፈሬ ባለትዳርና የልጆች አባት ጫት ዋና ምክንያት (factor) እንደ ነበረ ሁሉ በውል እረዳለሁ፡፡

ከራሱ ከሀይቅና አካባቢው በብዙ ኩንታል የሚገመት ወይም "በአይሱዙ" መኪናዎች ሊጫን የሚችል ጫት በየቀኑ ወደ ደሴ ከተማ እየተጓጓዘ የውሀ ሽታ ሆኖ (ተቅሞ) እንደሚያድር አውቃለሁ፤ እህል መብላታቸውን አቁመው ጫት ብቻ መመገብ የጀመሩ እስኪመስል ድረስ፣ ኪስን በሚያራቁት ዋጋ ጫት የሚገዙ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ አውቃለሁ፡፡ በባሕር ዳርም ሆነ በጎንደር ከተሞች የሚቅሙ ሰዎችና የመቃሚያ ቤቶች ቁጥር እንዲሁም የጫት ዋጋ ከጊዜ ወደ ጊዜ ስለማሻቀቡ መረጃ አለኝ፡፡ በባህር ዳር የአንድ ኪሎ ጫት ዋጋ 300 ብር መድረሱን በቅርቡ ሰምቻለሁ - የጥሩ ነጭ ጤፍ የኪሎ ዋጋ 15 ብር በሆነበት ከተማ!

የሀይቁ "የመዝናኛ" ቦታ የጫት ቃሚዎች ትእይንት በጣም ያስገረመኝና ተአምር የሆነብኝ የጫት ቂምሀ የቡድን ስራ መሆኑም አይደለም፡፡ በጣም አስገራሚው (አስቀያሚውም) ነገር አደባባይ የመውጣቱ ጉዳይ ነው፡፡ እስከማውቀው ድረስ የጫት ቂምሃ የቤት ውስጥ ጉዳይ ነበር - ቢሻው ከግለሰቦች ቤት ወይም ከሱቅ ይቃም፣ ቢሻው ከጫት ወይም ከሺሻ ቤቶች ይቃም፡፡ ይህ ደግሞ ያለ ነገር አልሆነም፤ እጅግ በርካታ ሰዎች መደበኛ ቃሚ ሆነው ሁሉ እያለ በይፋ እየቃሙ በአደባባይ መታየት አይፈልጉም፡፡ ቂምሀቸውን ሳያገባድዱ፣ ከሚቅሙበት ቦታ እንዲንቀሳቀሱ የሚያደርግ ጉዳይ ቢገጥማቸው የሚወዱትን ጫት የግዳቸውን ተፍተውት ይሄዳሉ (በደንብ ተጉመጥምጠውና የጫት ፋና እንዳይታይ ጥርሶቻቸውን ጭምር በደንብ አፅድተው)፡፡ አዎ - በተአምር እየቃሙ አይሄዱም፡፡ ለምን ጫት የአደባባይ ጉዳይ አይደለም፡፡ ጫት መቃም ጋር የተሳሰረ ሀፍረት አለ፤ የተሳሰረ ይሉኝታ አለ፡፡ ጫት ባብዛኛው የአደባባይ ክዋኔ አይደለም፤ በተለይም ለወጣቱ፡፡

አሁን ግን ያውላችሁ፣ ለጎ ሀይቅ ዳርቻ ላይ የአደባባይ ትእይንት ሆኗል - ጫት በአደባባይ መቃሙ፣ በይፋ ማመንዠጉ ማሳፈሩ ቀርቶ፣ በደቦ የሚከወን ምግባር ሆኗል፡፡ ለዚህም ነው ባየሁት ትእይት መደንገጤ፡፡ የምጠይቅባቸው አፍ የለኝም እንጂ አፍ ኖሮኝ በትህትና "ሜዳ ላይ ስትቅሙ ትንሽ አታፍሩም" ብላቸው ኖሮ ምን እንደሚመልሱልኝ አውቃለሁ ወይም ቢያንስ ቢያንስ እገምታለሁ "እኛ ምንም ጣጣ የለንም!" እኔም ቢያንስ በልቤ እንዲህ ማለቴ አይቀርም "ድንቄም ጣጣ የለንም! ድንቄም ጣጣ የሌለው ትውልድ!"

ጫት ሱስ አስያዥ ተክል ነው፡፡ "እንዳልደበር" ወይም "ከጓደኞቼ ጋር ለመጫወት" በማለት ወይም በሌላ ምክንያት በሳምንት አንድ ቀን መቃም የጀመረን ወጣት ቀስ በቀስ ወደ በሳምንት ሁለት ቀን ቃሚነት ያሸጋግረዋል፡፡ በሳምንት ሁለት ቀን በማስቃም ትንሽ ካቆየው በኋላ ቀስ ብሎ በማዋዛት ወደ በሳምነት ሶስት ቀን ቃሚነት… እያለ እያለ መደበኛ የቀን ቃሚ ያደርገዋል፡፡ በዚህም ሳያቆም "የጀበና" ቃሚነት (ረፋድ ሰአት ላይ የሚቃም) ደረጃ ያደርሰዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ትልቁ ችግር ፊት ወደ ነበረበት ("ኢ-ቃሚነት") መመለስ አለመቻሉ ነው፡፡

ጫት የሚቅም ሰው የሱስ እስረኛ ነው፡፡ የሱስ እሰረኛነት፣ ጣጣው ሀራራ (ጫት የመቃም ፅኑ ፍላጎት) ብቻ አይደለም፡፡ ሱሰኛነት (የጫት፣ የመጠጥ…) መንፈስንም ጉልበትንም ነው የሚያስር፤ አእምሮንም ህሊናንም ነው የሚሸባብ፣ የሚያደነዝዝ፡፡ ሱስ ወኔን ሽባ የሚያደርግ፣ የጥንካሬን መንፈስ የሚገድል በደም ውስጥ የሚረጭ መርዝነው፡፡ ያ የሱስ እስረኛ ደሙ ትኩስ የሆነው፣ አዲስ ነገር ለመስራት መንፈሱ የሚቋምጠው ወጣት ሲሆን ደግሞ ብዙ ነገሮች ይበላሻሉ፡፡ በጫት ሱስ ተለክፎ፣ የጫት ሱስ እስረኛ የሆነ ወጣት እንዴት ብሎ ነው የሀገርን ትልቅ አደራ ሊሸከም የሚችለው?…

የመጀመሪያውን "መዝናኛ" ቦታ አልፈን ከሀያ ሜትር በማይበልጥ ርቀት ላይ ወደሚገኘው ወደ ሁለተኛው መዝናኛ ቦታ አቀናን፡፡ የአሳው "ደንበኞችን" ጋሻው ያለው እዚያ ነው፡፡ "ምናልባት ቦታ ብናገኝ፣ የተሻለ ሁኔታም ካለ" በማለት ወደ እዚያው ከልጆቼ ጋር አመራን፡፡

ቢራውም አለ፤ ምንጣፉም አለ፤ ጫቱም አለ፤ ሲጋራውም አለ፤ ወጣቶቹም አሉ - ጠጪዎቹ፣ ቃሚዎቹ፣ አጫሾቹ፡፡ እዚያኛው የሌሉ ነገሮችም እዚህ አሉ፡፡ ይሄኛው መዝናኛ ቦታ እዚህም እዚያም ጉብ-ጉብ ያሉ ማስተናገጃ ጎጆዎችና የተለያየ መጠን ያላቸው ድንኳኖች አሉት፡፡ ወጣቶቹ ጎልማሶቹ፣ ወንዶቹ ሴቶቹ ከየጎጆዎቹና ድንኳኖቹ ውስጥ ተሰግስገው በመቃም፣ በመጠጣት፣ በማጨስ ላይ ናቸው፡፡ በእነሱ ቋንቋ "አለማቸውን እየቀጩ" ነው፡፡ በጣም ጥቂቶች ደግሞ - ልክ እንደ መጀመሪያው "መዝናኛ" ቦታ - መሬት ላይ አንጥፈው በግላጭ እየቃሙ ነው፤ ጣጣ የሌለው ትውልድ፡፡

በሁለቱ ቦታዎች ያየሁትን ብልሹነትና የሞራል ዝቅጠት ደምሬ ሳስበው ከዚያ አካባቢ ሮጬ ብወጣ ደስ ባለኝ፡፡ ሆኖም ቃል የገባሁላቸው ልጆቼ ከጎኔ አሉ፡፡ እናም የወንዙን ዳርቻ አካባቢ በመከተል ከሁለተኛው "መዝናኛ" ውስጥ የምንቀመጥበት ቦታ መፈለግ ያዝን፤ ሆኖም ቦታ የለም - ይሄኛውም "መዝናኛ" ቦታ በአንድ በኩል ጥንድ-ጥንድ በሆኑ በሌላ በኩል በቡድን-በቡድን "በተደራጁ" ቃሚዎችና ጠጪዎች ተወሯልና፡፡ ወደ መሀል ዘለቅን፤ አረፍ ብሎ ለመስተናገድ የምንቀመጥበት አንድም ቦታ አጣን፤ ቦታው ሁሉ ተይዟል ወይም ተወሯል፡፡

ለዚህ ሁሉ የሞራል ዝቅጠት ተጠያቂው ማን ነው? ራሳቸው የድርጊቱ ፈፃሚ ወጣቶችና ጎልማሶች? የቂምሀውንና የመጠጡን "ሜዳ" ያመቻቹት የመዝናኛ ቦታዎቹ ባለቤቶች? ይህን እያየ "ጆሮ ዳባ ልበስ" ያለው የከተማው አስተዳደር? ልጆቻቸውን በወጉ ኮትኩተው ያላሰደጉ ወላጆች? የሀይማኖት መምህራን?… መጠኑ የሚለያይ ካልሆን በስተቀር - ጠያቂ የለም'ንጂ ጠያቂ ቢኖር- ሁሉም የየራሱን ድርሻ ማንሳቱ አይቀርም፡፡

ተስፋ ቆርጠን እየወጣን እንዳለን ጋሻው ጋር ድንገት ተገናኘን፡፡ ብዙም አልረሳኝም፤ ፈጥኖ አስተወሰኝ፡፡ አሳ ልጋብዛቸው ልጆቼን ይዤ ብመጣም ቦታ በማጣታችን ልንመለስ መሆኑን ነገርኩት፡፡ "ጎጆ ልስጣችሁ" አለኝ፡፡ ጎጆውን የሚቅም ወይም የሚጠጣ ሰው የማይጋራን መሆኑን ጠይቄው ስላረጋገጠልኝ ወደ እዚያው አመራን፡፡ መጠነኛ ስፋት ያለው ሲሆን አሮግ ያሉ የፕላስቲክ ስጋጃዎች ተነጥፈውበታል፡፡ ወንበርም ሆነ ጠረጴዛ የለውም፡፡ ያው አንዱ የመቃሚያ ክፍል ነው ማለት ነው፡፡ እዳፈቀደው! ብቻ አሁን ልጆቼን ያስተናግድልኝ፡፡

ጋሻው ለጎጆው ብቻ አንድ መቶ ስድሳ ብር አካባቢ መክፈል እንዳለብን ነገረኝ - የአገልግሎት ክፍያ መሆኑ ነው፡፡ ይህን ሲሰሙ "ክፍያው አግባብ አይደለም" በማለት ልጆቼ መመለስን ብቸኛ አማራጭ አድርገው አቀረቡ፡፡ "እስከመጣን ድረስ…" በማለት ላግባባቸው ብሞክርም በሀሳባቸው ፀኑ…

በአንድ ፊት ሁለት መልክ ያላት ለጎ ሀይቅ ይህን ትመስላለች፤ ባዘቦቱ ቀን ጭምት፣ የተረጋጋችና ፍስሀን የምትቸር ሀይቅ! በረፍት ቀናት ደግሞ ረፍትን የምትነሳ፣ ጨርቋን ጥላ የምታብድና ፀጥታን የምትቃማ ሀይቅ! ወይም እንዲያ እንድትሆን የተፈረደባት ሀይቅ!

በረፍት ቀናት ወደ ሀይቁ "ለመዝናናት" የሚሄድ አንድ ወጣት ሀሳቡን በግጥም መግለፅ ካለበት እንዲህ ብሎ መቀኘት ሳይኖርበት አይቀርም

"ለጎ ሀይቅ ወርጄ፣ ጫቴን ልጎስጉሰው
ለጎ ሀይቅ ዘልቄ፣ መጠጤን ልጋተው
"ባንቻሮ-ባንቻሮ፣ እንዴት ይሞታል ሰው፡፡"

## የ ግ ጥ ም ጥ ግ

### ባለምንም ተስፋ

ከዚህ ቀደም ነበር

ወንዳፍራሽ ተብየው

ማዶና ላይ ሄዶ ጠላ የጨለጠዉ

አዕምሮው ደፍኖበት

ስሜቱ ሲብላላ

ወይዘሪት ቆንጆ ነሽ

በአቻ ተገፈፍ

የነገ ራዕይዋን

አላማዋን ስታ

የአመት ድከሟን

ለደቂቃ ስሜት

ርግፍ አርጋ ረስታ

በ love ስትሬቱ

አንድ ሁለት እያሉ

በበግተራው ስፍራ

የቁም ሲታገሉ

እንዲሁ በትዝብት

ቆሜ ያየኋቸው

ዘመነኛው አባት

መረብ ላከባቸው

ዳግመኛ ላይፈቱት

አጥብቆ አሰራቸው

ወንድነት ይመስል

"ሽከሽክኳት" እኮ ብሎ ሲያቅራራ

ብልጥነት መስሏታል

"አውጣሁት" እኮ ብላ ስታወራ

ይሄ ጉዳቱ

በደቂቃ እርካታ አንዱን ተሸክማ

ኑሮ ትኖራለች ባለምንም ተስፋ፡፡

በአረጋዊ ሰለሞን AS

# ድብብቆሽ

በሂሩት አድማሱ

የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነጽሁፍ ት/ክፍል - የስነጽሁፍ መምህርት

nanihira@gmail.com

ሚኪ በለጥሻቸው የላከችለትን ደብዳቤ በሰከነ መንፈስ ለማንበብ የመኝታ ቤቱን በር ቆልፎ አልጋው ላይ በጀርባው ተንጋለለ፤ በለጥሻቸው ጐረቤቱ ነበረች በሁለት ዓመት ዕድሜ የሚበልጣት በክፍል ደረጃም እንደዚያው የሚያስከትላት አብሮ አደጉ፣ የልጅነት ጊዜው ቁልጭ ብሎ ይታየው ጀመር፡፡ ድብብቆሽ ሲጫወቱ፣ በፊልም ላይ እንዳዩት አባራሪና ተባራሪ ሆነው ከእንጨት በተሰራ ሽጉጥ ሲተኳኮሱ ሁሉ ታየው፤ ፈገግ አለ፡፡

ከሀሳቡ እንደምንም ነቅቶ በእጁ የያዘውን ደብዳቤ ለማንበብ ሞከረ፡፡ የበለጥሻቸው የዓረፍተ ነገር አጀማመር፣ ‹‹ምን ብዬ ውስጤን እንደምገልፅ አላውቅም፡፡ እጅግ ከባድ የሆነ ህይወት አሳልፌያለሁ፤ ህይወት ለእኔ ሙሉ በሙሉ በማጣት የተሞላች ናት ማለት እችላለሁ፤ ልጅነታችን ፍቅርና ደስታ የተሞላ ነበር፡፡ ወደ ሁለተኛ ደረጃ ስናልፍ ግን ሁሉ ተቀየረ ከእኔ በትምህርት ደረጃ ስለምትቀድመኝ ብዙ ነገረ ቀድመህ አወቅህ፤ ፈለግህን ተከተልኩ አንተ አታውቅም እንጂ እኔ የሁልጊዜ ተከታይህ ነበርኩ፡፡ ከልጅነት አቆጥቁጣ የነበረችው ፍቅር አድጋ ነበር፡፡ ለኔ የውበት መመዘኛና መለኪያ ነበርክ፡፡ አንድም አልገባህም ጠዋት ከቤት ስትወጣ ከት/ቤት ከጓደኞችህ ጋር ስትቃለድ ስከታተልህ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ከሁለት አመት አልዘለለም ምንም ያህል ብወድህ አንተን ሌላ ከማፍቀር ልገድብህ አልቻልኩም፡፡

አዎ! ሀና የምትባል የክፍልህን ልጅ እንደወደድክ ሰማሁ፤ በፍቅር ቀን ከሌሊት እንደምታነባ፣ እሷ ደግሞ እንደማትፈልግ ሳይ አዘንኩ፡፡ እንደማፈቅርህ ቃለ አውጥቼ ባልነግርህም ባህላችን፣ ይሉኝታና ያለን ቤተሰባዊነት ገድቦ ቢይዘኝም ሁሉ ነገሬ ግን መልዕክት ነበረው፡፡ ፈገግ ስትል ሳይህ መፍገጌ፣ እያንዳንዱ ነገርህን መከታተሌ ፍላጎቴን ገላጭ ነበር፡፡ አንተ ግን አልተመለከትከውም ወይም ችላ ብለኸዋል፤ አላውቅም፡፡ ጭራሽ ለምትወዳት ልጅ መልዕክተኛህ አደረከኝ፡፡ አንተ ተቸግረህ ማየት፤ ውዬ ማደር ስለማልችል ቃልህን ይዤ አሳካሁልህ፡፡ በውስጤ ግን ምናለ እኔን እንዲህ በወደደኝ አልኩ፡፡ መጀመሪያም የማንገጥም ነን መሠለኝ ይህ ሁኔታ አልተፈጠረም፡፡

አንተ እኔን እንዳላየኸኝ ሁሉ እሷም አንተን አላየችህም፡፡ ለጊዜው ነፃ ስለሆንኩ ልሞክረው በሚል ፈቃደኝ እንደሆነች ገለፀችልኝ፡፡ መጥቼ ነገርኩህ ደስ አለህ፡፡ እኔም በሀዘን ውስጥ ደስታህን ተጋራሁ፡፡ ፍቅራችሁ የጋራ አልነበረምና ብዙ አልዘለቃችሁም በአጭር ተለያያችሁ፡፡ ቆይተህ ስትነቃ በትክክል የምትፈልገውን ነገር አወቅህ፡፡ ብዙ አንተን በመጠበቅ የዛለው ልቤ ግን ለሌላ የኔን ፍቅር ለሚሻ ሳይወድ ተሰጠ፡፡ የዚያኔ ወደ እኔ ለመምጣት ብትሞክርም የሰጠሁትን ቃል ግን ለማጠፍ አልቻልኩም፡፡ ይሁን እንጂ ውስጣዊ እኔነቴ የወደደውና መለኪያ ያደረገው አንተን ስለነበር አብሬ የሆንኩትን ሰው ልወደው አልቻልኩም፡፡ እንዳንተ ንግግሩ አይጥመኝም፤ እንዳንተ አካላዊ አቋሙ አይስበኝም፤ እንዳንተ አለባበሱ አይማርከኝም ሚኪ የምለው ይገባሃል? እስከሞቴ አፋፍ እወድሀለሁ፡፡ ››

ሚኪ ደብዳቤውን አንብቦ መጨረስ አቃተው ወረቀቱን ከደረቱ ላይ ልጥፍ አድርጐ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ፡፡ ‹‹በለጥ እጅግ በጣም እወድሽ ነበር እኮ፤ ለእኔም መለኪያዬ ነበርሽ አጠገቤ ሆነሽ ሌላ አንቺን ስፈልግ ኖርኩኝ ያለእርካታ ህይወትን ገፋሁ አገባሁ ልጆች ወለድኩ፡፡ በለጥዬ በሞት አፋፍ ብትሆኚም እንኳን እጅግ እወድሻለሁ ምን ላድርግ፡፡›› ብቻውን እንደ እብድ ሲያወራ ቆይቶ ወደ ደብዳቤው አይኑን መለሰ፡፡ ከአልጋ ላይ ቀስ ብሎ ተንሸራቶ ወርዶ ወለሉ ላይ ተንበርክኮ ንባቡን ቀጠለ፡፡

‹‹እናም ሚኪ ካንተ ሌላ ህይወትን ለማጣጣም ብሞክርም አቃተኝ፡፡ አንተ የሌለህበት አገር ለመኖር ርቄ ሄድኩ፡፡ ግን ብቻዬን አልነበረም አንተን ይዤ እንጂ በመጨረሻም ተመለስኩ አድራሻህ፣ ኑሮህ ተለውጧል፡፡ የድሮ ወዳጆቻችን እንደፈለከኝ አግኝተው ነገሩኝ፡፡ ብዙ ርቄ ከሄድኩ በኋላ በመሆኑ ምንም ውጤት አላገኘህበትም፡፡ ሚኪ ድክመታችን በግልፅ ሌላውን ነገር እንደምናወራ ሁሉ ስለ ፍቅር ህይወታችን አለማውራታችን ነበር፡፡ ይህም ትልቅ ዋጋ አስከፍሎናል፡፡

ዛሬ ይህን ደብዳቤ የፃፍኩት ሳንተ በማሰብ ነው፡፡ ሴት ልጆች አሉህ፤ ወንዶችም፡፡ መደባበቅ የማያዋጣ ኪሳራ ያለበት ነውና ልጆችህን አስተምራቸው፡፡ ፍሬማ ከማይኮንባቸው መንገዶች ውስጥ አንዱ ግልፅነት ማጣት ነውና በግልፅ ማንኛውንም ጉዳይ ከቤተሰብና ከጓደኞቻቸው ጋር እንዲያወሩ ምከራቸው ይህን የምለው ያንተ የሆነውን ስለምወድና ያንተ ማንኛውም ነገር እንዲጎዳ ስለማልፈልግ ነው፡፡ ዛሬ በተያዝኩበት የጨጓራ አልሰር ህመም ህይወቴን ለማጣት በአፋፍ ላይ ብሆንም ለማንም እጅ ያልሰጠው ልቤ ዛሬም ይወድሃል፡፡ እስከመቃብር እወድሃለሁ ከቻልኩ ከመቃብርም በኋላ ደህና ሁንልኝ፡፡›› ሚኪያስ አነባ ሆዱ እጅግ ባባ፡፡ በሩ ተንኳኳ አባብዬ ክፈትልኝ፡፡ በለጥሻቸው ነበረች፣ የመጀመሪያ ልጁ፡፡ ዕድሜ ልኩን የሚወዳትንና ፍቅራቸውን ተገላልጸው ባለመነጋገራቸው ያጣትን የልጅነት የጐረቤቱ ልጅ ማስታወሻ፡፡ ልቡ አልጨከነም በሩም ከፍቶ እቅፍ አደረጋት፡፡ ‹‹በለጥዬ በጣም እወድሻለሁ፡፡ ይቅርታ አድርጊልኝ በድዬሻለሁ፡፡›› በለጥሻቸው ግራ ግራ ተጋባች፡፡ አባቷ ሲያለቅስ ስታይ የመጀመሪያዋ ነው፡፡ በጣም ትወደዋለች፡፡ ከስራ ተመልሶ እቤት ሲገባ ተከታትላ ታጫውተዋለች፡፡ ከሱ ጋር ተጫውታ አትጠግብም፡፡ የዛሬው ሁኔታው ግን ከወትሮው ተለይቶባታል፡፡ ‹‹አባባ ምንም አላደረከኝም፡፡ እኔም እወድሃለሁ አታልቅስ፡፡ የሆንከውን ንገረኝ፡፡ እማዬ የት ናት?›› ገጽታዋ ወዲያውኑ በሃዘን ጠቆረ፡፡ ሚኪ ‹‹እሺ ልጄ! ምንም አልሆንኩም፡፡›› እንባውን ጠራርጐ ልጁን አቀፈ፡፡ የዕድሜ ልክ ፀፀት በውስጡ እንደያዘ አስተውሎ ለጊዜው ዝም አለ፡፡

# የ ግ ጥ ም ጥ ግ

## ምርቃት

<u>አሜን በሉ</u>

አገርን ሰላም፣

ተማሪን ዶርም ያሳድርልን፡፡

ማንነትን ትቶ፣
ባህልን ረስቶ ከመሮጥ ይቆጥበን፡፡
የኛን ፍቅር፣
የፔዳን ፍርፍር ይጨምርልን፡፡
እጃችን ታጥበን፣
አባይን ገድበን እንድንበላ ያርገን፡፡
ኢትዮጵያ ወደን፣
አንድ አፍቅረን ለመኖር ፅኑ ያርገን፡፡
ቦርሳችን በዶላር፣
ሆዳችን በማር ይሙላልን፡፡
ከሳምንት ፍቅር
ከገበያ ግርግር ያውጣን
የበሶ በረከቱን፣

የተማሪ ውጤቱን ይጨምርልን፡፡

ለመምህራን ብቃትን፣
ለካፌ ምግብ ጥራትን ይጨምርልን፡፡
“A”ን ወደ ፊት

“F”ን ወደኋላ ያርግልን፡፡
በግ ተራ ከመገተር፣
ከኢቦላ በሽታ፣
ከትናነሲ ጫጫታ ይሰውረን፡፡
ከሎከር በሶ፣
ከ6 ኪሎ ድንች፣
ከመዲና ጠላ አይለየን፡፡
ሰውን እንደ ራስህ፣
ኢትዮጵያ እንዲቅርስህ፣
እንድትወድ ያርግህ፡፡
ከፔዳ ተመርቀህ
ከጠላት ርቀህ፣
ለመኖር ፈጣሪ ይርዳህ፡፡
የሽንት ቤት ሽታን፣
የኢቦላ በሽታን፣
በዱር በገደሉ ይስደድልን፡፡

መልካሙ ከፋለ 2ተኛ ዓመት
የጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ተማሪ

## ለካስ

የነገር ዝልዝል ጥብስ፣
የወሬም ቡፌ አለው፣
አሉም ብቃት ሆኖ
ፈላጊ ሰው አለው፣
ለካስ.............፣
ይሄም ችሎታ ነው፡፡

## ሠው

ታምኖ የሚኖረው፣
ቃሉን ማያጥፈው፣
ለኔ ሙሉ ብቁ፣
እሱ ብቻ ነው ሰው!

በነብዩ ንጉሴ

# ቄንጠኛው (ልብወለድ) ክፍል 5

ከባለፈው እትም የቀጠለ

አረጋዊ ሰለሞን 𝒜𝒮 (3ኛ ዓመት የጋዜጠኝነትና ተግባቦት ተማሪ)

Aregawi solo27@gmail.com/Aregawiosolomon @FB.Com/Aregawi Solomon Blogspot.com

## እሁድ ማታ 12፡45 ዋናው ግቢ ባህል ማዕከል

ቄንጠኛው ቀን ሲያነብ የዋለውን «ባለዕዳ» ከተሰኘው አጭር ተውኔት የተወሰደና ከገፀ ባህርያቶች መካከል «ታዳጊው» የተሰኘውን ዓብዪ ገፀ ባህርይን መድረክ ላይ ወጥቶ ይተውናል፡፡ የታዳጊው ታሪክ ስለ አንድ ጎጃም ውስጥ በምትገኝ «መሸንቲ» በምትባል አካባቢ ተወለዶ በትንሽዬ ደሳሳ ጎጆ ውስጥ እየኖረ የተማረና በኋላም የScholarship ዕድል ገጥሞት ሃርቫርድ ዩኑቨርሲቲ ውስጥ ትምህርቱን አጠናቅቆ ለብዙ ዓመታት እዚያው የኖረና ለዚህ ስኬቱ መሰረት የሆነችውን ሃገሩን ያልረዳ፤ የኋላ ኋላ ግን ለአገሩ አንዳች ነገር ባለማድረጉ የተፀፀተ «ባለ ዕዳ ነኝ፡፡» እያለ ዘወትር ራሱን የሚወቅስ ጉልማሳ ላይ ያጠነጥናል፡፡

የታዳጊው ገፀ ባህርይ ዋነኛ ሚናም ይኖርበት ከነበረው ሃርቫርድ ዩኒቨርሲቲ ወደ ቀድሞው ሃገሩ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ እያስተማረና ያደገበት የቀዬው ማህበረሰብ በተግባር ሲረዳና ሲታደግ ባሳለፋቸው በርካታ ጊዜያት ሃገሩን ባለመርዳቱ ሲፀፀትና ዩኒቨርሲቲው ውስጥ ላሉት ተማሪዎቹን ለልቡ እያስተማረ ሲመክር ያሳያል፡፡

በመድረኩ ፊት ለፊት ባሉት ወንበሮች ላይ የተቀመጡ የተውኔቱ አካላት የታዳጊውን ታሪክ ከቄንጠኛው የአተዋወን ብቃት ጋር እያመሳከሩ በተመስጦ ይመለከቱታል፡፡

ቄንጠኛው ትወናውን ቀጠለ «አንቺ ባለፀጋዋ መፃጉዕ እማማ.... ምንም እንኳን ዓይኔ በባዕድ ቁሶች (ህንፃዎች) ተጋርዶ ቢንቀዋለልም ምስኪኑ ልቤ ግን ያ ያሳደገኝን ደሳሳ ጎጆሽን አይረሳም፡፡ ይሄው ልመጣልሽ ነው እናት ሃገር አዎ አሁኑኑ መምጣቴ ነው፡፡ እናም እባክሽን እጆችሽን ዘርጊልኝ እባክሽን ያ ፈዋሹ ያሳደገኝ አፈርሽን ልሳለመው፡፡ እባክሽን ፍቀጅልኝ እባክሽን እናት ዓለም........»

አያና በክበቡ ከሚሳተፉት ‘አማተር’ ተዋኒያን መካከል አንዱ ነው፡፡ ብዙ ጊዜ ካነበባቸው የተለያዩ ይዘታዎች ካሉዋቸውን መፅሐፍት ያውጣጣቸውን ድርሰቶችና አልፎ አልፎም የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ከሚያሳዩአቸው ተግባራትና ከነባራዊው ሁኔታ ጋር እያዛመደ አዳዲስ ፅሁፎችን በመፃፍ ይታወቃል፡፡ ብዙ ጊዜ ሀገር የሚሸቱ ፅሁፎችን እየፃፈ ተዋኒያኑን ያሰራቸዋል፡፡

ማዕከሉ ላይ ቲያትር በሚሰሩበት ወቅት ለጊዜውም ቢሆን ቄንጠኛው አለባበሱን ማስተካከል እንዳለበት ስለተነገረውና ጠንቅቆም ስለሚያውቅ ያስተካክላል፡፡

የማዕከሉ የቲያትር ልምምድ ሰኞ፣ እሮብና ዓርብ ቢሆንም አሁን እየተሰሩት ያለውን ቲያትር ግን ከወትሮው ለየት ያለና ሰፋ ያለ ጊዜ ስለሚያስፈልገው ከሁልጊዜው በተጨማሪ እሁድም የመስሪያ ቀናቸው አድርገዋታል፡፡

ልክ ልምምዳቸውን እንዳጠናቀቁ ሰኞ በሰዓታቸው መገናኘት እንዳለባቸው ተነጋግረው ተለያዩ፡፡ አያና እና ቄንጠኛው ዶርማቸውም አንድ ላይ በመሆኑና ፍላጎታቸውም ከሞላ ጐደል ተመሳሳይ ስለሆነ የግል ወሬአቸውን እያወሩ ጉዞአቸውን ወደ ዶርም አቀኑ፡፡

ድንገት በወሬአቸው መሃል ላይ የቄንጠኛው ስልክ ጮኸ፤ ስልኩን አነሳና ወደ ጆሮው በማስጠጋት ድምፁን ቀነስ አድርጎ ጥቂት ካወራ በኋላ ስልኩን ዘጋው፡፡

«TG ደግሞ ማን ናት?» አለ አያና ቄንጠኛው ስልክ ሲያወራ«TG» ሲል ሰምቶት ኖሯል፡፡

«አንዲት ቀሽት የሆነች አዲስ ሚስቴ ነች፡፡» አለው ቄንጠኛው የወንድነት ስሜቱን እያንፀባረቀ፡፡

«መቼም ያገኘሃቸውን ሁሉ እስኪሰለቹህና እስክትቀይራቸው ድረስ ማሞገሱን ልምድህ ሆኗል፡፡ ይችም ያው ስትሰለችህ.....»

«አይ TGዬ እማ መቼም ቢሆን አትሰለቸኝም፡፡ አቤት ውበት! በዚያ ላይ የከንፈሮቿ ልስላሴ አስማት ነው የሆኑብኝ፡፡ እንደውም አሁንም ብትመጣ ከንፈሮቿን በከንፈሮቼ እየማግኩኝ ባሳይህና ብደሰት! ቆይ ለምን አሁን ጠርቻት እየላስኩኝ አላሳይህም?» አለው ቄንጠኛው እጁን ወደ ኪሱ እየከተተ፡፡ ሞባይሉን (ተንቀሳቃሽ ስልኩን) ለማውጣት በመፈለግ፡፡

«አባቴ እሷን አጥቼ ግቢ ውስጥ ከምኖር እሷን ይዤ በረንዳ ባድር እመርጣለሁ፡፡ ሌላው ቢቀር አይበርደኝም፡፡ plus to that last night እንኳን ስስማት ማንም አልከለመንም፡፡ ለዛም አስሜ ያን ያክል እየቀወጠው፡፡»

«አስመላሽ ደግሞ ምን አደረገ?»

«ምን ያደርጋል ደግሞ ግቢው ላይ ወረደበት እንጅ፡፡ ‘ጀለሴ’.... የለለ ጠጥቶ ብሶቱን አላወጣም መሰለህ፡፡ አቦ እናቴን ተመቸኝ፡፡”

«ማለት ግቢውን አማረረው እያልከኝ ነው?» አለው አያና

«አማረረው ብቻ! ከአትክልቶቹ ጀምሮ በሱቅ አድርጐ ላውንጅን ጨምሮ ባለስልጣኖቹን አልሸረደዳቸውም!»

«ይሄውልህ ቄንጠኛው አስመላሽ ቢኖር ደስ ባለኝ፡፡ እንደ አጋጣሚ ግን የለም፡፡ ነገር ግን አንተንም ሳይህ ከሱ ሃሳብ ጋር የተጋራህ ይመስለኛል፡፡ እስኪ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ፤ ስለዚህ ግቢ ይህን ያክል አቃቂር የምታወጣበት ምን ከፍቶህ ነው፡፡ ሌሎቹን ግቢዎች ብታያቸውስ ምን ይውጥህ ነበር?! በርግጥ እንደፈለክ የምትቦርቅበት ነፃነት ልታገኝ ትችል ይሆናል፡፡ በእርግጥም ታገኛለህ፡፡ ነገር ግን ያ ነገር እንዳንተ አካሄድ የሚጠቅምህ ይመስልሃል? እንዴ አንተ እዚህ ግቢ በመግባትህ እኮ ቤተሰቦችቸም ተረጋግተው እንደሚኖሩ ማወቅ አለብህ፡፡ ሠላም ነዋ ዋናው ነገር፡፡ ሰላም ከሌለ የህሊናም የአካልም እፎይታ ስለማይኖር ጤና አይኖርም ማለት ነው፡፡ አንተም ሰላማዊ ቦታ ላይ በመኖርህ ማመስገን አለብህ፡፡ ሌላውን አካል ከመተቸትህ በፊት ደግሞ ራስህን መመርመር አለብህ፡፡ እስኪ እንደው የምትጠቀምበት መፀዳጃ ቤት እንኳን እየው! እንሰሶች የሚኖሩበት ይመስላል? ያሳፍራል፡፡ የምንኖርበትን ዶርም እንኳን ማፅዳት ሳንችል ሌላውን ስትተቹ ትንሽ አይከብድም፡፡ በእርግጥ ብዙ ብዙ ችግሮች እንዳሉ ይገባኛል፡፡ ነገር ግን ቅድሚያ እኛ የራሳችንን ችግር እናስተካክል ከዚያም የሚመለከተውን አካለ ችግሩን ነግረነው አብረን ብንፈታ ወደር የሌለው ስኬት ይሆናል፡፡ ጉድፍህን ሳታይ የሌላውን መመልከትና መሳለቅ ግን ይደብራል፡፡» አለው አያና፡፡ ይህንን ሁሉ ሲያወሩ ዶርም ደርሰው ኖሯል፡፡ በሩን ከፍተው ገቡና አልጋ አልጋቸው ላይ ተጋደሙ፡፡

## ሰኞ ጥዋት 2፡10 የመማሪያ ክፍል ውስጥ

ወንበሮቹ ለፈተና በሚመች መልኩ በአራት ረድፍ ተሰድረዋል፡፡ ጥቃቅን የአጤረራ ወረቀቶች የያዙና ለፈተና ዝግጅት ያላደረጉ ተማሪዎች አንዳንድ ነገሮችን ለማድረግ የጥግ ወንበሮቹን መርጠዋል፡፡ በተሳትፎአቸው ሻል ያሉት ደግሞ መሃል ላይ እና ፊት ያሉት ወንበሮች ላይ ተቀምጠው አስተማሪያቸው አቶ ጌትነት ቻላቸውን ይጠባበቃሉ፡፡ መምህር ጌትነት ቻላቸውም ጋዎናቸውን ለብሰው የፈተና ወረቀቶችን ይዘው ከተፍ አሉ፡፡

ቄንጠኛው ለፈተና ዝግጅት ባለማድረጉ ሸመታ (ኩረጃ) ካገኘሁ በማለት መሀል ላይ ካሉት ተሳታፊ ተማሪዎች ጋር ተቀምጧል፡፡ መምህር ጌትነት የፈተና ወረቀቱን ከመበተናቸው በፊት በርከት ያሉ ማስጠንቀቂያዎች ተናገሩ፡፡

«I don’t need anyone to cheat. All of you should have to do your own. Otherwise, you will pay the consequence. Put all your papers on the ground. If you have any question, just raise your hand.»

ይህንን ካሉ በኋላ የጥያቄ ወረቀቱን መበተን ጀመሩ፡፡ ተማሪዎቹም ፈተናቸውን ጀመሩ፡፡ ክፍሉ በዓይኑ ይቀላውጣል፡፡ ከፊሉ እጁ ላይ፣ ወረቀት ላይ.... የፃፈውን አጥሬራ ላይ ያፈጣል፡፡ ጥቂቶችም አንገታቸውን እያስረዘሙ ፊደላትን ይለቅማሉ፡፡ በጣም ጥቂቶቹም መልሱ ከላይ ይወርድ ይመስል ወደ ጣሪያው ያንጋጥጣሉ፡፡ ሌሎቹም እንዲሁ ጥያቄ ወረቀቱ ላይ እየተመለከቱ ይፅፋሉ፡፡ መምህር ጌትነትም ፊት ለፊት ላይ ከተቀመጡበት ወንበር በመነሳት እየዞሩ መመልከት ጀመሩ፡፡

ማስታወሻነቱ ለእነ ሰለሞኖች ይሁንልኝ፡፡ ይቀጥላል!!!

## ውድ የናይል ጋዜጣ አንባቢያን

የናይል ጋዜጣን ተነባቢነት ለማሳደግ የዝግጅት ክፍሉ የተለያዩ ስራዎችን እየሰራ ይገኛል፡፡ እርስዎም አስተማሪ እና አዝናኝ የሆኑ

- የተለያዩ ጹሁፎች
- ማህበራዊ ሳይንሳዊ ኢኮኖሚያዊ እና ቴክኖሎጂ ነክ ጉዳዮች
- የካርቱን ስእሎች
- ቀልድ
- ግጥም

እና የመሳሰሉትን አዲሱ ጥበብ ህንጻ 5ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር G5-02E በሚገኘው ቢሯችን ድረስ በመምጣት ወይም በኢሜል gracetsegi@gmail.com ይላኩልን፡፡

በናይል ጋዜጣ በቀጣይም ለእናንተ ይመጥናሉ ያልናቸውን የተለያዩ ጽሁፎች ማቅረብ እንደምንቀጥል እየገለጽን ለቀጣዩ ወር ዕትም ጽሁፍ ማበርከት የምትፈልጉ ሁሉ በአድራሻችን መላክ ወይም በኢሜል አታች ማድረግ የምትችሉ መሆኑን በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

ዝግጅት ክፍሉ

# ስብጥረ-ባህል (Cultural Diversity)

**ተመስገን በየነ**

የፎክሎር (የባህል ጥናት) ትምህርት ክፍል መምህር

E-mail:- folkloreculturebdu@gmail.com

ውድ አንባቢያን ለቀረበው ርዕሰ ጉዳይገላጭ የሚሆኑኝን ቃላት በእንግሊዝኛ እና በአማርኛ የተሰጣቸውን ተለምዷዊ ፍች፣ ትርጓሜና ጽንሰ ሃሳቡ ምን እንደሚመስል እንደሚከተለው እጠቁማለሁ፡፡

“Diversity” የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል በአማርኛ ስብጥር/የ…ዓይነት ብዛት የሚለውን ትርጓሜ የሚይዝ ይመሥለኛል፡፡ በተወሰኑ ተቋማት፣ ምሁራንና ግለሰቦች “Diversity” ለሚለው “ብዝኀ” የሚል የአማርኛ ትርጓሜ በመስጠት ሲጠቀሙበት ይስተዋላል/ይደመጣል፡፡ ለዓብነት ያህል “Bio-Diversity” የሚለውን “ብዝኀ ሕይወት”(?)፤“Cultural Diversity”ን ደግሞ “ብዝኀ ባሕል”(?) በማለት አቻ ትርጓሜ ይሰጡታል፡፡

“ብዝኀ” የሚለው የአማርኛ ቃል “በጥሬው” ወይም በቀጥታም ሆነ በአውዳዊ ፍችና ትርጓሜው “Diversity” የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ፅንሰ ሃሳብ፣ ትርጓሜና ፍች ይሰጣል የሚል አመኔታ የለኝም፡፡ በኪዳነውልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ መዝገበ ቃላት ሐዲስ (ገጽ ፪፻፶፱/259) “ብዝኀ” ማለት “ብዛት፣ ብዙነት፣ ብኸር/መብዛት፣ አበዛዝ፣ ብዙ፣ እጅግ አያሌ” የሚል ነው፡፡ በደስታ ተክለወልድ (1962፣፻፶፯/157) መዝገበ ቃላት “በዝኀ/ብዝኀ” ማለት “ፈደፈደ፣ ተረፈ፣ ከልክ አለፈ፣ ረባ፣ በረከተ፣ ዐየለ፣ በረታ፣ ወለደ፣ ከበደ” እንደ ማለት ነው፡፡ከዚህ አንጻር “ብዝኀ” ማለት የአንድን ነገር መዋለድ፣ መራባት፣ መባዛት፣ መብዛት፣ መበርከት፣ ብዙ ሆኖ መገኘትን እና የመጠንና የቁጥር መብዛትን የሚያመለክት ነው (ለምሳሌ ከዕፀዋት አይነት አንድ ባህር ዛፍ ወስደን ከሃያ ዓመት በኋላ መቶ ባህር ዛፍ ቢሆን የባህር ዛፍን ብዝኀነት/ብዙነት በቁጥር በማጤን ብዝኀ ማለት እንችላለን)፡፡

ስብጥር ማለት የአንድን ነገር በቀለም፣ በመጠን፣ በዝርያ ወዘተ መሰባጠር እና መለያየትን የሚያመለክት ነው (ለምሳሌ በአንድ አካባቢ የሚገኙ ዕፀዋት በቅርፅ፣ በዓይነት፣ በቀለም፣ በመጠን፣ በዝርያ ወዘተ ይለያያሉ፤ ተሰባጥረው በአንድ አካባቢ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ዕፀዋት ስብጥረ ሕይወት ይባላሉ፡፡ ስብጥር ሲባል በአንድ በተከለለ አካባቢ የአይነት እና የቁጥር ብዛትን አጣምሮ ሊይዝ ይችላል)፡፡


ከዚህ አንፃር ስብጥረ-ባህል (Cultural Diversity) ማለት በአንድ አገር መልከዓምድራዊ ክልል ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦችን የባህል፣ የቋንቋ፣ የፆታ፣ የብሔር፣ የቀለም ወዘተ ስብጥርና ልዩነትን መሰረት ያደረገ ትርጓሜና ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ አጭር ጽሑፍ ውስጥ በእንግሊዝኛ “Cultural Diversity” ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ ስብጥረ-ባህል የሚለውን የአማርኛ አቻ ፍችና ትርጉም በወጥነት ተጠቅሜያለሁ፡፡ ለአብነት ያህል፡- ከዚህ በታች የቀረበው ፎቶ ግራፍ ስብጥረ ባህል (በቋንቋ፣ በብሔር፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በሐይማኖት፣ በአለባበስ…) በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል ይጠቁማል፡፡

## 1.1 የስብጥረ ባህል ዓይነትና መገለጫ

በአለማችን ስብጥረ-ባህል (Cultural Diversity) ጎልቶ ከሚታይባቸው አገሮች መካከል ህንድ፣ ናይጄሪያ እና ኢትዮጵያ በቀደምትነት ይጠቀሳሉ፡፡ በእነዚህ አገሮች የሚገኙና የሚኖሩ ህዝቦችን ስብጥረ- ባህል መለያ እና መገለጫ ዓይነቶች ጠቁሞ ከማለፍ ውጭ ለመዘርዘር ያዳግታል፡፡ ስለሆነም በወፍ በረር የስብጥረ-ባህል ዓይነትና መገለጫዎችን እንደሚከተለው ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡

ከስብጥረ-ባህል ዓይነትና መገለጫዎች መካከል ባህል (በጥቅሉ)፣ ቋንቋ፣ ፆታ፣ ብሔር፣ ጎሳ፣ ቀለም (አካላዊ መልክ)፣ ታሪክ፣ አመጋገብ፣ አለባበስ፣ ሐይማኖት፣ እሴት (values)፣ እምነት (Belief)፣ ሥርዓተ ከበራ (Rituals)፣ ባህላዊ ትዕምርት/ውክልና (Cultural symbols)፣ ሃገረሰባዊ ልማድ (Social Folk Customs)፣የባህል ውርስና ቅርስ(Cultural Heritage)፣ ቁሳዊ ባህል፣… ይጠቀሳሉ፡፡ በለተይ የሰው ልጆች የሕይወት ተመክሮ (Humans life Experience)፣ ቡድናዊና ግለሰባዊ አመለካከት (Groups’ and Personal Attitudes)፣ መልክዓ ምድራዊ ልዩነት (Geographical difference)፣ ሀገር በቀል እውቀት (Indigenous knowledge)፣ አለማዊና መንፈሳዊ አተያይ (Secular and Spiritual View)፣ የቤተሰብ የኑሮ ሁኔታ/ደረጃ፣ ማኅበረ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ (Socioeconomic status)፣ የትምህርት ደረጃ፣ ግላዊና ቡድናዊ አስተሳሰብ እና ፍላጎት ወዘተ የሚሉት ዋና ዋናዎቹናቸው፡፡

አንዳንድ ምሁራን የስብጥረ-ባህልን ዓይነት በተለያየ አኳኋን ለመመደብ ይሞክራሉ፡፡ ለዓብነት ያህል፡-




## 1.2 ስብጥረ-ባህል እና “ሕንጸተ” ሰላም (Cultural Diversity and Peace Building)

ከሁለተኛው የአለም ጦርነት በፊት ስብጥረ ባህል (Cultural Diversity) የእድገት፣ የልማትና የሰላም ተግዳሮት ተደርጎ ይታሰብ ነበር፡፡ አንድ አይነት ብሔር፣ ቋንቋ፣ ሐይማኖት፣ ቀለም፣ ባህል ወዘተ. ያላቸው አገሮች ለእድገት፣ ለሰላምና ለልማት የተመቹ አንጻራዊ ሰላም የሰፈነባቸው፤ ማኅበራዊ ግንኙነታቸውና ፖለቲካዊ አስተዳደር ሥርዓታቸው የዳበር ብሔራዊ መግባባትና አንድነታቸው የጠነከር ታላቅ አገርና “ኀያል” መንግስት መመስረት የሚችሉ ተደርጉ በአወንታዊ መልኩ ሲቀነቀን እና ሲሰበክ ኖሯል፡፡

በአንጻሩ ስብጥረ ባህል፣ ቋንቋ፣ ሐይማኖትና የተለያዩ ፍላጎትና አስተሳሰብ ያለባቸው አገሮች የተረጋጋ ሰላም፣ “መቻቻል”፣ አንድነትና መግባባት የሌለባቸው ጠንካራ አገርና መንግስት መመስረት የማይችሉ ተደርጎ ይገለጻል፡፡ ከዚህ እሳቤ ብዙም ሳንርቅ አገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ በአገር ውስጥ እና በውጭ አገር ኃይል በሺ ቤት የሚቆጠሩ ጦርነቶችን አካሂዳለች/ አስተናግዳለች፡፡ ለዚህ ጦርነት እና የሰላም እጦት መሰረታዊ መንስኤ የስብጥረ ባህል እና የቋንቋ ልዩነት ይሆን? አይመስለኝም! ጥቂት አስተዋጽኦ ሊኖረው ይችላል፤ መሰረታዊ ምክንያት ይሆናል የሚል አመኔታ ግን የለኝም፡፡ ጥያቄውን ለታሪክ ምሁራንና መሰል ተመራማሪዎች እተዋለሁ፡፡ አንባቢያንም የራሳችሁን ተመክሮ (Experience) እና ተብሰልስሎት በማከል እንድታጤኑት እጠይቃለሁ፡፡

በአንጻሩ አንድ አይነት ዘር፣ ብሔር፣ ቋንቋ፣ ሐይማኖት፣ ቀለም፣ ባህል ወዘተ ቢኖረን ታላቅ አገር እና መንግስት መስርተን የዓለም ቁንጮ እንሆን ነበር? ይህም ጥያቄ የመላሹን አዕምሮ፣ ተብሰልስሎት እና ቁዘማ ይደቃል! ከ1950ዎቹ መለስ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እየዳበር፣ የሰው ልጅ አስተሳሰብ እየተለወጠ፣ ዘመናዊ የአኗኗር ሥርዓት እየመጣ የዓለም ምስጢር እና ሕብር በየሙያ መስኩ እየተመረመር እና እየተጠና መጥቷል፡፡ በዚህ ዘመን ስብጥረ ባህል ያሉባቸው አገሮች ለቡድንና ለግለሰብ መብት ትኩረት የሚሰጡ፣ ለባህል መከበር፣ ለሕንጸተ ሰላም (Peace Building) መስፈን፣ መከባበር፣ መደማመጥ፣ መረዳዳት ወዘተ ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በሰላምና በመተጋገዝ ለመኖር፣ የሥራ ፈጠራን ለማዳበር፣ ልማትንና እድገትን ለማምጣት እና ለማጠናከር፣ የወል ታሪክ ለመስራትና የጋራ ሐብት ለማፍራት፣ አንድነታቸውን እና ሕብርነታቸውን ለመጠበቅ ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳለው ዩ.ኔ.ስ.ኮ/የተባበሩት መንግስታት የሳይንስ፣ የትምህርትና የባህል ድርጅት/ (2001G.C) ይጠቁማል፡፡

ኢዮጵያውያን በሐይማኖት፣ በቋንቋ፣ በባህል… ተወራርሰው፣ ተቃይጠው፣ ተሰባጥረው፣ ተከባብረው፣ ተፋቅረው፣ በሰላምና በደስታ ዓመታትንና ዘመናትን በአንድነት ኖረዋል፡፡ ተዛምደዋል፣ ተዋልደዋል፣ ተጋምደዋል፤ ኧረ እንዲያውም! “አፍንጫ ሲመታ…” ይባላል፡፡ ለአድዋ ሞተዋል፣ ለዐባይ ገብረዋል/ዘምረዋል፣ ለአክሱም፣ ለላሊበላ፣ ለአልነጃሺ መስጅድ፣ ለአባገዳ…ኧረ ስንቱ! የኢትዮጵያዊነት አሻራችን፣ የልከተ ስሬት/ፍጥረት ጥንስስ/መቋጫ እንብርታችን… ይመስሉኛል፡፡ ኢትዮጵያውያን “ተቻችለው” አልኖሩም! “መቻቻል” ማለት እርስ በራሳቸው ተጠባብቀው፣ አንዱ ያንዱን ባድማ እና ታሪክ ሳይቋደስና ሳይነካ የኖሩባት፣ ባይነ ቁራኛ እየተያዩ፣ እየተጠባበቁ፣ እየተዘባበቱ ዘመናትን ያስቆጠሩባት፤ ሲያስፈልግ እንደ ዘመድ ሳያስፈልግ እንደ ጥላት ሆነው አገር ያቀኑባት አይደለችም፡፡ ጧት ማታ “የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ተቻችለው፣ አብረው ለመኖር ተፈቃቅደው…” ሲባል ምን ማለት ይሆን(?) ተቃይጠን፣ ተዋልደን፣ ተደባልቀን፣ የዘር ሃረግች ስራችን ተዋርሶ (ከዓያት አያልፍም…) ምን ዓይነት ታሪክ ለመስራት ነው “የምንቻቻለው”፡፡

ህዝቡ ይህን እሴት፣ ሕብር፣ አንድነት እና አብሮ የመኖር ምስጢሩን፣ ታሪክና ጥበቡን የሚመረምርለት እና የሚያጠናለት ባለሙያ፤ ባህል፣ ቋንቋ፣ ቅርሱን… የሚጠብቅለት፣ ለመጭው ትውልድ የሚያስተላልፍለት፣ የሚያከብርለት፣… አስተዳዳሪ መንግስት እና የዘርፍን ባለሙያ ጥረት፣ ተግባር እና ክህሎት ይፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሚገኙ ህዝቦችን ባህል፣ ቋንቋ፣ ታሪክ ወዘተ የሚያሰባስብ፣ የሚያደራጅ፣ የሚተነትን… ባለሙያና ተቋም በቀበሌ፣ በወረዳ፣ በዞን፣ በክልልና በአገር ደረጃ ማቋቋም አይነተኛ መፍትሔ ይመስለኛል፡፡ ስብጥረ-ባህልነት በጊዜና በዘመን ቀስ በቀስ እየተለወጠና እየተቀየረ ይሔዳል፡፡ እለት በእለት ካልተሰበሰበ፣ ካልተደራጀ፣ ካልተተነተነ ፋይዳነቱ ይከስማል/ሐብትነቱ ይጠፍል፡፡ በወግና በስርዓቱ ካልተያዘ “በእጅ የያዙት ወርቅ…” ከሆነብን ከሰማኒያ በላይ የምንለው ቋንቋ፣ ባሕል፣ ታሪክ… እንደ ጧት ጤዛ ታይቶ ይጠፋል፡፡

**ቸር ያሰንብተን!!!**

# Call for papers

## The 33rd May Annual International Educational Conference

## May 8-9, 2015 Bahir Dar, Ethiopia

**"Education is the most powerful weapon you can use to change the world" Nelson Mandela.**

The Faculty of Educational and Behavioral Sciences, Bahir Dar University, seeks submission for its**33rd Annual International May Educational Conference**,taking place from **May 8-9, 2015** at the Peda Campus Auditorium in Bahir Dar, Ethiopia. The general theme of the conference is **QUALITY EDUCATION FOR SUSTAINABLE DEVELOPMENT**. Quality education develops people's knowledge, skills and competencies to achieve their potential as human beings and members of society. It is also an essential instrument for enhancing all dimensions of sustainable development. The Conference provides a platform for researchers, policy makers and practitioners to discuss and share research outcomes and experiences on the role of quality education for sustainable development. Thus, the 33rd Annual International May Educational Conference Organizing Committee welcomes quality papers and posters on the following topics ***by relating to the general theme of the conference***.

- *Adult education*
- *Education and economic development*
- *Education and psycho-social issues*
- *Education policy and strategy*
- *Education and environment*
- *Education, inclusion, equity and diversity*
- *Educational leadership and management*
- *Higher education*
- *Indigenous knowledge*
- *Learning and teaching*
- *Lifelong learning*
- *Quality education*
- *National qualification framework*
- *Teacher education*

***Note:*** Papers which are not directly related to these topics may also be submitted for consideration.

**Key Dates:** March 1, 2015: Deadline for full paper submission

March 15, 2015: Decisions regarding submitted papers

May 8-9, 2015: The Conference

**Contact Information & Sending Address:**

- Faculty of Educational and Behavioral Sciences, Bahir Dar University, P.O.Box 79, Bahir Dar, Ethiopia

- Tel No: 251 (582) 205931; Fax: 251 (582) 205932; E-mail: mayconference1@gmail.com; Website: www.bdu.edu.et/febs

- To avoid postal delays, we encourage submission via the email address.

**Remember**: Decisions regarding submitted papers and posters will be communicated by email.. There is no registration fee.

- The University will cover accommodation and local transport cost, and pays a modest honorarium for papers and posters selected and presented.

- Selected papers may be considered for possible publication on Bahir Dar Journal of Education

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ